ተወዳጁ ሩሚ

https://t.me/z_bishara

Edit with WPS Office

"ባንተና በሁሉ ነገር መካከል ያለው ድልድይ ፍቅር ነው"

"እውቀት እንደ ዛፍ ሲሆን፡ ስር እና ግንዱ መካ፡ ቅርንጫፎቹ መዲና፡ ቅጠሎቹ ዒራቅ፡ ፍሬዎቹ ደግሞ ኹራሳን ይገኛሉ" የተባለው ንግርት ሐቅ ሆኗል። ኹራሳን (በዘመናችን ኢራን፣ አፍጋኒስታን እና መሀከለኛውን እስያ ሀገራት ያካለለች ነበረች) በአራት ሰፋፊ ግዛቶች የተከፋፈለች ስትሆን ኒሻፑር፣ በልኽ፣ ሄራት እና መርቭ ይባላሉ። ቡኻራ እንዲሁም ሰመርቀንድ ኹራሳን ውስጥ የሚካተቱ ሁለንተናዊ የስልጣኔ ማማ ላይ የደረሱ ግዛቶች ነበሩ።

የሐዲስ ኢማሞች ቡኻሪ፣ ሙስሊም፣ ቲርሚዚ፣ አቡ ዳዉድ፣ ነሳኢ እና ኢብኑ ማጃህ...ታላላቅ የእስልምና ምሁራን እና ሀዳሲያን ሑጀቱል ኢስላም አቡ ሓሚድ አልገዛሊ፣ አብደላህ ኢብኑ ሙባረክ፣ አልጁወይኒ፣ አቡ መንሱር ማቱሪዲ፣ ኢብራሂም ኢብን አድሃም፣ ፈኽሩዲን ራዚ...ታዋቂ ሳይንቲስቶች ኢብኑ ሲና፣ አልቢሩኒ፣ ዑመር ኸያም፣ አልኸዋሪዝሚ፣ ድንቅ ገጣሚያን ፊርደውሲ እና ጃሚ... ኹራሳን እነዚህን ሁሉ ያፈራች የከዋክብት መፍለቂያ ነበረች። ረቢዓል አወል 6፣ 604 ዓ.ሂ ደግሞ በልኽ ውስጥ (አሁን ምዕራብ አፍጋኒስታን) ጀላሉዲን ሙሐመድ በልኺ(ሩሚ) ተወለዱ። መውላና ሙሉ ስማቸው ሙሐመድ ኢብኑ ሙሐመድ አልሑሰይን አልኸጢቢ አልበልኺ አልበክሪ ሲሆን የሰዪዲና አባበክር አስ-ሲዲቅ ዘር ናቸው። አፍቃሪነታቸውም ከቅድመ አያታቸው የወረሱት ሳይሆን አይቀርም። "እርሳቸው ሲጠጡ እኔ ረካሁ" እንዳሉት ሲዲቁ! ሰዪዱል ዓሺቂን እየተባሉ የሚጠሩት መውላና ጀላሉዲንም የፍቅርን ዜማ ለዓለም ያሰሙ ረቂቅ ባለቅኔ ናቸው።

Edit with WPS Office

በተወለዱበት ምድር መጠራት የብዙሃኖች መለያ በመሆኑ ሙስሊሞች ዘንድ በልኺ ተብለው የሚጠሩት እኚህ የፍቅር አቀንቃኝ ምዕራባውያን ሩሚ ይሏቸዋል። ይኖሩበት የነበረው የአናቶሊያ ግዛት ሙስሊሞች እጅ ከመግባቱ በፊት በቤዛንታይን/ሮማ ስር ስለነበር በቅርብ ዘመን የመውላና አድናቂ የሆኑት አውሮጳውያን በዚሁ ስያሜ መጥራትን መርጠዋል። ለሁሉም ነብይ የራሱ አቡበክር አለው፡ ለእየሱስ የራሱ ሃዋሪያቶች እንደነበሩት እኔም የራሴ ደርዊሾች ይኖሩኛል። በምሥራቁ ሞቼ በምዕራብ እነሳለሁ" ብለው ከዐረቡ ዐለም በላይ ምዕራባውያኑ በእርሳቸው መለኮታዊ ብዕር እንደሚጠቃቀም አስቀድመው ተናግረውታል። ጀላሉዲን ደግሞ ካበረከቱት አስተዋፅኦ ወይም ተግባራቸው ታይቶ የተሸለሙት ማእረጋዊ ስም ነው፡ የዲን ክብረት፣ ግርማ እንደማለት...

የታላላቅ ዓሊሞች፣ ፉቀሃዎችና ሳይንቲስቶች መኖርያ የነበረችው ኹራሳን በርካታ የተሰውፍ ሊቃውንትን ማፍራት ችላለች። አቡ ኢስሓቅ ኢብራሂም በልኺ (ኢብን አድሃም)፣ አቡ ዓሊ ሸቂቅ በልኺ እና አቡ አብደላህ ኢብን ፈድል በልኺ በዘመኑ ተጠቃሽ የነበሩ የተሰውፍ መምህራን ነበሩ። የመውላና ጀላሉዲን አያት ሑሰይን ኢብን አሕመድ እና አባታቸው ሙሐመድ በሃኡዲን ከተለያዩ ሩቅ ስፍራዎች እየመጡ እግራቸው ስር ጎንበስ ብለው እውቀትን የሚቀስሙ በርካታ ተማሪዎች የነበሯቸው ክቡራን ሊቃውንት የነበሩ ሲሆን አባታቸው 'ሱልጣኑል ዑለማእ' የሚል ኩንያ የተሸለሙ ቀላል ሕይወትን የሚመሩ እውቅና ድንቅ አርአያ ነበሩ።

Edit with WPS Office

ፍቅር ማለት፦

አላህ "ሁሉን ላንተ ስል ፈጠርኩ" ሲልህ

አንተ ደግሞ "ሁሉን ላንተ ስል ተውኩ" ማለትህ ነው

13ኛው ክ/ዘመን

በእስልምና ታሪክ ውስጥ ትልቁ ክስተትና የለውጥ መነሻ የሆነው ሂጅራ ካለፈ ሰባት ምዕተ-ዓመታት ተቆጥረዋል። በርካታ ሀይማኖታዊ፣ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፓለቲካዊ ስኬቶች እና ጉድለቶች ተመዝግበዋል። በመጀመርያዎቹ ቅን ኸሊፋዎች ዘመን ነበር በዓለማችን ገናና የነበሩት ኃያላን መንግስታት ድል የተመቱት - ሮም እና ፐርሺያ። እስልምናም ከዐረብ ሀገራት ባሻገር መስፋፋቱን ቀጥሏል። አስተዳደሩ በፖለቲካ በኩል አንድ ጊዜ ሲዳከም ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲጠናከር ቀናት እና ዘመናት ሲገለባበጡ ከርመዋል። መስቀላውያን 'ቅዱስ ጦርነት' አውጀው ለዓመታት ሙስሊሞችን ሲያዳክሙ ቆይተዋል። በጊዜው የነበረው የኡመያውያን አስተዳደር የቁልቁለት ጉዞ ላይ ነበር። ሌላው ትልቁ ስጋት ደግሞ በጄንጊዝ ኻን የተመሰረተው ምስራቃዊው የሞንጎላውያን መንግስት በ13ኛው ክ/ዘመን (እ.ኤ.አ) በርካታ ግዛቶችን ከሙስሊሞች ነጥቋል።

ሞንጎላውያኑ በታጠቁ ወታደሮችና ጦር መሳርያ ባልያዙ ሰዎች መሀከል አይለዩም። ህፃናት፣ ሴቶችና አቅመ-ደካሞችን አይምሩም። ከፊትለፊታቸው ያገኙትን የሰው ዘር በሙሉ ይጨፈጭፋሉ። የአምልኮ ስፍራዎችን፣ መድረሳዎችን እና የተለያዩ ተቋማትን ሙሉ በሙሉ ያወድማሉ፤ ከተሞችን ያፈራርሳሉ፤ ሰፋፊ ግዛቶችን የመቃብር ስፍራ

Edit with WPS Office

ያደርጋሉ። የኸዋሪዝም 12 ከተሞች፡ የመርቭ ሰባት ከተሞች ወድመው ብዙሃን ዜጎች በቅፅበት ታርደዋል። በተመሳሳይ ቡኻራ፣ ሰመርቀንድ፣ መርቭ፣ ኒሻፑር እና ሌሎች ግዛቶችን ተቆጣጥረዋል። ሞንጎላውያኑ ኒሻፑር ላይ በሙስሊሞች አስክሬን ፒራሚድ ሰርተው ነበር ድላቸውን ያከበሩት።

በምስራቅ በኩል የሞንጎላውያን ኃይል እየበረታ መምጣት እና ከበልኽ ገዢ ጋር በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት በሃኡዲን በ1213 (እ.ኤ.አ) የትውልድ ከተማቸውን ተሰናብተው ወጡ። መድረሻው ያልታወቀ ፍፃሜው ያልተገመተ ስደት...ህፃኑ ሩሚ ገና የአምስት ዓመት ለጋ ነበሩ። እትብታቸው የተቀበረበትን ከእኩዮቻቸው ጋር የቦረቁበትን ሜዳ ሸንተረር መሰናበት ለብላቴናው ሩሚ አሰዛኝ የሕይወት ውሳኔ ነበር። ጉዞው አድካሚ፣ መንገዱም በተለያዩ ጠላቶች ተከብቦ አስጊ ቢሆንም ሌላኛዋ የኹራሳን ግዛት ኒሻፑር የመጀመርያ ማረፊያቸው ሆነች። ታላቁ የፐርሺያ ገጣሚ ዑመር ኸያም እዚሁ ኖሯል፣ ታዋቂው የሱፊ ባለቅኔ ፈሪዱዲን አጣር ኒሻፑር መገኛው ነበረች።

ትንሹ ጀላሉዲን በስደት መንገዳቸው ላይ በኪባር ዓሪፎች ተዘይረዋል። ፈሪዱዲን አጣር ሩሚ እና አባታቸውን በሃኡዲን ልጅ ኋላ አባት ፊት ሆነው ሲጓዙ ቢያዩ "ያ አላህ ጥራት ይገባህ! ውቅያኖሱን ከኩሬው ጀርባ የምታስከትል ጌታ" ብለው ተደምመዋል። ተደምመው ብቻ አልቋጩትም፤ ለዘመናት የለፉባቸውን ስራዎች (ዲዋን ፈሪዱዲን አጣር እና ሌሎች የጥበብ ድርሳኖችን) በአህያ አስጭነው ጀባ ብለዋቸዋል። የሩሚ አባት "ገና ልጅ አይደል ወይ?" ብለው ጠየቁ አልተባለም። ልጃቸውን አሳምረው ያውቁት ኖሯልና። ትንሹ ሙሐመድ አባቱን የሚበልጥ ዓሪፍ እንደሚሆን ራሳቸው ይተነብዩ ነበር።

Edit with WPS Office

ሱልጣኑል ዑለማእ በሃኡዲን ኒሻፑር ውስጥ የተወሰኑ ጊዜያትን ከተቀመጡ በኋላ ወደ በግዳድ ተጓዙ። በግዳድ መልካም አቀባበል ተደረገላቸው። ንጉሱ ወኪሎቹን ልኮ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክት እና ስጦታዎች ከገንዘብ ጋር አበረከተላቸው። ወደ ሸንጎ ይምጡ ሲልም ትእዛዝ ብጤ መልእክት ሰደደ። "ሊያገኘኝ ከፈለገ ፍርድ ቤት ሳይሆን ጁሙዓ ቀን ጀማዓ መስጂድ ይምጣ" ብለው የተላከላቸውን ስጦታዎች መቀበል እንደማይፈልጉ በትህትና ነግረው መለሱ። ጁሙዓ ደርሶ የበግዳዱ ንጉስ መስጂድ ገባ። በሃኡዲን በሰዎች ሀብት/ንብረት ዙርያ የሚከተለውን አካሄድ ማስተካከል እንዳለበት፣ አናናሩን አላህና መልእክተኛው ወደ ሚወዱለት ዘይቤ መቀየር እንዳለበት መከሩት። ይህ ካልሆነ ግን ከሞንጎሎች ጥቃት መትረፍ አዳጋች መሆኑን አስጠነቀቁት። በግዳድ ብዙም ሳይቆዩ ለሐጅ ፍጻሜ ወደ መካ ተጓዙ። ከዚያም ሶሪያ...ላሪንዳ...እያሉ በርካታ ሀገራትን በስደት አዳረሱ።

ጀላሉዲን እና በሃኡዲን ከሀገር ሀገር ሲዛወሩ ምድር ጸሐይን 13 ጊዜ ጠውፋለች። በየሀገራቱ የሚፈራረቁት በጋና ክረምቶች ሳያደናቅፏቸው ደህና ማረፊያ ሲፈልጉ አያሌ ከተሞችን ገብተው ወጥተዋል። ሩሚ ተማሪነት ከጀመሩ ሰነባበቱ፡ አባት በሃኡዲን ከተማሪዎቻቸው መካከል ታማኝና ብቁ ለሆነው ቡርሃኑዲን ሙሸቂቅ ቲርሚዚ አስረክበው የልጃቸውን በእውቀትና ምግባር እነፃ ሂደት ይከታተል ዘንድ አደራ ብለዋል። ቁርኣን፣ ሱና(ሐዲስ) እና ፊቅህ ተማሩ። አያይዘውም ሒሳብ፣ ፍልስፍና፣ ፖለቲካ እና ግብረገብ አጠኑ። በዐረብኛ እና ፋርስ ቋንቋ የበቁ አዋቂ ለመሆንም ቻሉ። ኋላ ላይ በበርካታ ስራዎቻቸው ሩሚ እኚህ መምህራቸውን ሲያመሰግኑ ይስተዋላል።

Edit with WPS Office

የአንድ ሰው ብልህነት አልያም ሞኝነት ከልጅነቱ ይንፀባረቃል ይባላል። ጀላሉዲን ሩሚ ገና ከጨቅላነታቸው ጀምሮ አስተዋይና አሰላሳይ የነበሩ መሆኑን የሚያመላክቱ ክስተቶች ተነግረዋል። አንድ ጊዜ ከእኩዮቻቸው ጋር እየተጫወቱ ሳለ በመንደሩ የሚገኙ ቤቶች እርስ በርስ እጅግ ከመቀራረባቸው የተነሳ ልጆች ከአንዱ ቤት ጣርያ ወደ ሌላኛው እየዘለሉ ይጫወቱ ነበር። አንድ ልጅ ሩሚን ከቤታቸው ጣርያ ወደ ቀጣዩ ቤት እንዲዘሉ ገፋፋቸው። ጀላሉዲን በተረጋጋ መንፈስ እንዲህ አሉት፦

"ከጣርያ ጣርያ መዝለል የድመትና የውሻ ባህሪ ነው። ሰው መዝለል ከፈለገ ከፍታው ከምድር ወደ ሰማይ መሆን ይኖርበታል" ወደተሻለ መንፈሳዊ ማንነት ማደግ የሰው ልጅ ተልእኮ መሆኑን ማልደው የተረዱት ሩሚ ከዚህች ዓለም ወደ መጨረሻው ዓለም ሳይሰበሩ መሻገር መቻል ውጥናቸው ነበር። በቤታቸው ስለ እምነትና ስነ-ምግባር ከዓሊሞች ጋር የሚደረገው ውይይት ሩሚ ላይ ተፅእኖ ማሳደሩ ይነገራል።

ስደተኞቹ እስካሁን ሁነኛ ማረፊያ አላገኙም። ላሪንዳ ከተማ ሲደርሱ ጀላሉዲን ሩሚ 18 ዓመት ሞልቷቸዋል። አባታቸው ጁሃር ሃቱን የተባለች መልከ መልካምና ፀባየ ሰናይ ልጅ ዳሩላቸው። ከአንድ ዓመት በኋላ የበኩር ልጃቸው ሱልጣን ወለድ ተወለደ።

"ከሁሉ በላይ ገንዘብ ከመረጥክ ትሸሸጣለህ ትግገዛለህ፤ ለመብል ስስት ካለህ የዳቦ እህል ትሆናለህ፤ ይህ የማይካድ ሐቅ ነው። ያፈቀርከውን ትሆናለህ!"

Edit with WPS Office

አናቶሊያ

ምስራቃዊቷ ቱርክ በሰልጁቅ አመራር ስር የምትተዳደር ውብና ምቹ ግዛት ስትሆን ሱልጣን ዐላኡዲን ከይኩባድ ዓሊሞችን ወዳጅ፣ ሊቃውንትን አክባሪ ነበር። ከተለያዩ መንደሮች ዓሊሞችን እያደነ ኮንያ ያኖር ነበር። ስለ ሱልጣኑል ዑለማ በሃኡዲን እና ልጃቸው ሩሚ ኸበር ሲደርሰው ጊዜ መፍጀት አልፈለገም አፍታ ሳይቆይ የጥሪ ካርድ ላከላቸው። በ1228 ሱልጣን በሃኡዲን ከ22 ዓመቱ ጀላሉዲን ጋር ኮንያ መጥተው ከተሙ። ኮንያ ውስጥ ከሰከኑ ሁለት ዓመታት በኋላ የሩሚ አባት ወደ አኺራ ሄዱ። ቀደም ብለው እናታቸውን የቀበሩት ሩሚ ሐዘን ቢበረታባቸውም ሲቃውን ዋጥ አድርገው የአባታቸውን መድረሳ በ24 ዓመታቸው ተረከቡ። ሱልጣን ከይኩባድም ሆኑ ሌሎች ተማሪዎች መስፈርቱን ሁላ አሟልተው መድረሳውን ማስተዳደር ያለባቸው ጀላሉዲን መሆናቸውን ተስማምተዋል። አባታቸውን ሱልጣኑንም ሆነ ተማሪዎችን አላሳፈሩም። ሩሚ በአጭር ጊዜ ውስጥ አመርቂ ውጤት ማሳየት ጀመሩ። ዝናቸው በኮንያ ናኘ፤ ምሁርነት፣ አርአያነት፣ መልካም ስነምግባርና ቅንነት መታወቂያቸው ሆነ። ሀላፊነታቸውን በብቃት እየተወጡ ኮንያ ውስጥ ትምህርታቸው ተወዳጅ ለመሆን ጥቂት ጊዜያት ብቻ ነበር የፈጀው። ተማሪዎቻቸው በዙ፤ ለጥያቄ እና ውይይት ከሩቅ ስፍራ የሚመጡትም በረከቱ።

አንድ እለት በሙሪዶቻቸው ተከበው በፍቅር ምድጃ ዙሪያ ተሟሙቀው ባሉብት ወቅት አንድ ጥንብዝ ያለ ሰካራም ወደ ሐድራቸው ብቅ ይላል። መቀላቀሉ ሳያንሰው የሙሪዶችን ክልል አልፎ ከሰይድ ሩሚ ጎን ይዘናፈላል። እንደ ጨቅላ ህጻን በጀላሉዲን ቀሚስ ሥር ሲንፏቀቅ የመጠጡ ሽታ ሐድራውን አናወዘው፡ ሙሪዱን በንዴት አቅበዘበዘው። በሰካራሙ ድርጊት የተበሳጩት ተማሪዎች ለሰይዳቸው ክብር

Edit with WPS Office

አፀፋ ለመስጠት እያጉተመተሙ ብድግ አሉ።

የተማሪዎቻቸውን ግንፈላ ያዩት ሰይድ ሩሚ ቆጣ ብለው "የጠጣው ይህ ወጣት ነበር የሰከራቹት ግን የኔው ጉዶች እናንተው ናችሁ!" ብለው ሰካራሙን ስካሩ እስኪበርድለት ድረስ ጫፉን እንዳይነኩት አስጠነቀቋቸው።

እሳት በእሳት አይጠፋማ!

ጊዜያት ነጎዱ...መምህራቸው ቡርሃኑዲን ከሄዱበት ሲመለሱ በመውላና የትምህርት አሰጣጥ ተደሰቱ። በዐቂዳ፣ ግብረገብ፣ መንጢቅ፣ ፍልስፍና እና ስነ-ፅሑፍ ዘርፎች ምጡቅ እውቀት አላቸው። ከዒልም እርከን ትልቅ ደረጃ ላይ ደርሰዋልና አሁን ደግሞ መንፈሳዊ ተግባር ላይም መመንጠቅ ይኖርባቸዋል ሲሉ ወሰኑ። የተለያዩ ትእዛዛትን እየሰጧቸው ሲያሰለጥኗቸው ሩሚም በደስታ እየተቀበሉ ሲተገብሩ ዘጠኝ ዓመታት ተቆጠሩ። ለዘጠኝ ዓመታት የሩሕ ምግብ ከሸኻቸው እየተቀለቡ ደለቡ። በዘጠኙ ዓመታት መገባደጃ ሩሚ የሸኽ ቡርሃኑዲን ግልባጭ የሆኑ ያህል ተሰማቸው። በእሳቸውና በመምህራቸው መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የሌለ መሆኑ ታወቃቸው። እንዲህም አሉ፦

"ፈተናዎችን ሁሉ አልፈህ በሳል ሁን፤ ልክ እንደ ቡርሃን ሙሐቂቅ የወደብ መብራት ሁን፤ ራስህን ስትነቀንቅ ቡርሃንን ሆነህ ታገኛለህ። ባርነትህን ስታውጅ በርግጥም ንጉስ ሆነሃል"

አንድ ጊዜ ከተማሪዎቻቸው አንዱ መጣና እንዲህ አለ :- "መምህር ሆይ፤ በተደጋጋሚ ፈጣሪ በችግር እየፈተነኝ ነው፤ እንዳልሸነፍ ስጋት ያዘኝ"

ሩሚም:- "በእያንዳንዱ መነካትህ ተስፋ የምትቆርጥ ከሆነ ችግሩ ከፈጣሪ ሳይሆን

Edit with WPS Office

ከአንተ ነው፤ የፊት መስታወትህን ዘወትር ስታሽው የበለጠ እያበራና አጥርቶ እያሳየህ መምጣቱን እንዴት ዘነጋኸው?" በማለት መለሱለት። የሩሚ ምላሽ እዚህ ላይ ጥልቅና ታላቅ እውነትን ይዞ እናገኘዋለን። ችግር በሰው ልጅ ሲመጣ ሊያጠነክረን፣ ሊያበረታታንና ይበልጥ ራሳችንን እንድናይ ለማድረግ እንጂ ተሸንፈንበት ሕይወት በችግር ሲፈተን ተስፋ እንድንቆርጥ አይደለም። መስታወት ሲታሽ ይበልጥ እየነፃና እያማረ እንደሚመጣው ሁሉ የሰው ልጅም ሕይወት እንዲሁ ያማረ ይሆናል ማለት ነው። ሰው ከምንጣፉ ጋር ተጣልቶ አይደለም በዱላ የሚደበድበው፡ በውስጡ የያዘውን አቧራ ሊያፀዳለት እንጂ። አላህም ይበልጥ ሊያነፃን ሲፈልግ ነው ፈተናዎችን የሚያከታትልብን ወይም የሚያከብድብን። ሩሚ በዚህ መንገድ ነው ለሰዎች ግልፅ በሆነ መንገድ ሕይወትን የሚያስተምሩት።

ሁለት የጀላሉዲን ሩሚ ሙሪዶች ይጣሉና አንደኛው ሌላኛውን የሚያሳምም ንግግር ይናገረዋል። መውላና ሩሚ ስለጉዳዩ ሲያውቁ ሰዳቢውን ወደ መካ ሄዶ ካዕባን እንዲያፈርስ ይነግሩታል። ሙሪዱ በጣም ይደነግጣል። “እነ ሸህ እንዴት እንዲህ አይነት አስከፊ ነገር እንዳደርግ ያዙኛል?” ሲል ይጠይቃቸዋል።

ሩሚም “የልብን ካዕባ መጠበቅ ካልቻልክ፣ መካ ያለው ካዕባ ምን ይሠራልሃል?” ብለውታል። መካ ያለው ካዕባ በታሪክ ለበርካታ ጊዜያት ፈርሶ ተገንብቷል። ነገር ግን የልብ ካዕባ አንዴ ከፈረሰ ዳግም ላይገነባ ይችላል። የሙእሚን ቀልብ ደግሞ ከካዕባ ይበልጥ መከበር እና መጠበቅ እንዳለበት ያስተማሩት ረሱሉላህ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም ናቸው።

በዐቅልም በሩሕም የመጠቁት ሩሚ ሩጫዬን ጨርሻለሁ ብለው አልተቀመጡም። አሁንም ቢሆን እውቀትን ከመፈለግ ሳይቦዝኑ ሐለብ/ደማስቆ አራት ዓመታት ተማሩ።

Edit with WPS Office

ከአራት ዓመታት ቆይታ በኋላ በተማሪዎቻቸው ውትወታ ወደ ኮንያ ተመለሱ። ደረሳዎቻቸው እና ሕዝቡ በነቂስ ወጥተው ደማቅ አቀባበል አደረጉላቸው። ሽምሱዲን ኢስፋሃኒ የተባለ የሱልጣኑ ሚኒስቴር ቤተ-መንግስቱን ለሩሚ ስጦታ አበረከተ። ሩሚ ግን መድረሳቸውን መርጠው ሊቀበሉት እንደማይችሉ በትህትና ገለፁለት። ሩሚ አሁንም ከሸኻቸው የሚቀስሙት ትምህርት አላበቃም። የሚታዘዙትን መንፈሳዊ ተግባራት ኽልዋ እየገቡ ከሰው ተገልለው ዒባዳ ይፈፅማሉ። ለ120 ቀናት ከኽልዋቸው ቆይተው ሲወጡ ሸኽ ቡርሃኑዲን የወጣቱ ሩሚ ደረሳነት ማብቃቱንና ሌሎችን መምራት የሚችሉበት ደረጃ መድረሳቸውን አወቁ። የተማሩትን ሁሉ በሕይወታቸው እየተገበሩ ለሌሎችም መንገድ አመላካች መሆን ችለዋል። ከ34 ዓመታቸው ጀምሮ የኮንያ ሸኽ እና ኸጢብ ሆኑ። ቡርሃኑዲን ተልእኳቸውን ጨረሱ፤ በስተመጨረሻም በደስታ ተሞልተው ፈገግ እንዳሉ ከዚህች ዓለም ተለዩ። እጅግ ተወዳጅ በሆነው የትምህርት አሰጣጣቸው ሩሚ በአንድ ወቅት ከአስር ሺህ በላይ ተማሪዎች ነበሯቸው። እስልምናን ይሰብካሉ፣ ህዝቡን ወደ አላህና መልእክተኛው ይጠራሉ፣ ወጣቶችን በእውቀትና ምግባር አንፀው ይኮተኩታሉ...

ነገር ግን ስለ ግጥም አንዲትም ቀን አስበው አያውቁም ነበር። በዚሁ ሁኔታ ሶስት ዓመታት አለፉ...

"መንገዱን ስትጀምር ይገለጥልሃል"

Edit with WPS Office

የጠብሪዙ ጸሐይ

"ትናንት ባደርኩበት ቦታ ዛሬን አልደግምም፡ አከታትዬ በአንድ ሳህን አልመገብም። በየእለቱ አዳዲስ ፊቶችን መመልከት ያስደስተኛል። ከቦታ ቦታ እየተዘዋወርኩ ፍጥረተ-ዓለሙን እቃኛለሁ። አላህን ፍለጋ ምስራቅና ምዕራብን ዞርኩ፡ ሰሜንና ደቡብንም አካለልኩ። ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ገብቼ፣ እልም ካለ በረሃ ሰምጬ፣ ሜዳ ገደሉን አስሼ ዛሬን ደርሻለሁ። ከታላላቅ ዓሊሞች ጋር ተወያይቻለሁ፣ ለህፃናት የሚሰጠውን ትምህርት አድምጫለሁ፣ መድረሳ ውስጥ ከተማሪዎች ጋር ተፍሲር እና መንጢቅ ተወያይቻለሁ። ቤተ-መቅደሶችን፣ ገዳሞችን፣ ቅዱሳን ስፍራዎችን ጎብኝቻለሁ፣ ከባህታውያን ጋር ዋሻ ውስጥ ተቀማምጫለሁ፣ ከደረሳዎች ጋር ዚክር ብያለሁ፣ ከሀይማኖተኞች ጋር ጾሜ ከመናፍቃን ጋር አፍጥሬያለሁ። ከሁሉም ዓይነት እምነት ተከታዮች፣ በተለያየ የእድሜ እርከን ላይ ካሉ ሰዎች፣ በየዘርፉ ከተሰማሩ ሙያተኞች ጋር ቆይቼ የተፈጥሮ ሕግን አውቄያለሁ።

ሞት አያስፈራኝም። የሕይወት ፍፃሜ ነው ብዬ አላምንምና! እጀሌ እየቀረበ መሆኑ ሲታወቀኝ ግን ምድር ላይ አሻራዬን ሳላኖር ማለፍ አልፈለግኩም። ብዙ የምተነፍሳቸው ቃላቶች፣ በርካታ የማወራቸው ታሪኮች ውስጤ ታጭቀዋል። ይህን እውቀት ለሌላ ሰው ማስተላለፍ አለብኝ። ሸኽ ያልሆነ ተማሪም ያልሆነ እኩያ ጓደኛ እፈልጋለሁ። ዱዓ አደረግኩኝ፣ አላህን ወዳጅ ይሰጠኝ ዘንድ ተማፀንኩት። በግዳድ ባባ ዘማን ጋር እንድሄድ ተጠቆምኩ።

በግዳድ ባባ ዘማን የተባሉ ሸኽ ጋር ደርሼ እጅ ሳምኩ። "ሁሉን እውቀትህን ማስተላለፍ ትፈልጋለህ። ይህን እውነት እንደ ውድ እንቁ በመዳፍህ ጨብጠህ

Edit with WPS Office

እጅግ ለምታፈቅረው ሰው ትሰጣለህ። ነገር ግን የሰውን ልብ በመንፈሳዊ ብርሃን መክፈት ቀላል ስራ እንዳይመስልህ! በምላሹ ምን ልትከፍል አዘጋጅተሃል?" አሉኝ።

"እንገቴን ለመስጠት ዝግጁ ነኝ" ብዬ መለስኩላቸው"

"ፍቅር ማለት የነብያችን (ዓለይሂ-ሰላት-ወሰላም) መንገድ ነው"

ባባ ዘማን

"በግዳድ ይህ ሰው እንደሚመጣ ምንም ፍንጭ አልነበራትም፡ እኔ ግን ወደ ዛውያችን የመጣበትን ቀን በፍፁም ልረሳው አልችልም። የዛን ቀን ከሰአት እንግዶች ነበሩን፡ የከተማዋ ቃዲ (ዳኛ) ከባለሟሎቹ ጋር ሊጎበኙን መጥተዋል። እየተጨዋወትን ሳለን አንድ እንግዳ ከእኔ ውጪ ሰው አላናግር ብሎ ደጃፍ ላይ እንደቆመ ሲነግሩኝ እንዲያስገቡት ምልክት ሰጠኋቸው። ከላይ እስከ ታች ጥቁር የለበሰ፣ ረጅም፣ ቀጭን፣ የእድሜ ባለፀጋ ሰው ነው፡ እንደ አሊፍ ቀጥ ብሎ የሰለከከ አፍንጫ፣ እንደ ሬንጅ ጠቁረው ወደ ውስጥ የተሸሸጉ አይኖች፣ በወፍራሙ ተገምድለው አይኑ ድረስ የተዘናፈሉ ጥቁር ፀጉሮች። ረጅም ባለቆብ ካባ፣ የሱፍ ቀሚስ እና ከበግ ቆዳ የተሰራ ጫማ የለበሰ ሰው በሩ ደጃፍ ቆሟል፡ ከእንጨት የተሰራ ጎድጓዳ ሳህን በእጁ ይዟል፡ ሐኪም ደርዊሾች የነፍሳቸውን ከንቱነት እና ባዶ ጉራ ለማስቀረት ከሰዎች ምፅዋት የሚቀበሉባት ሳህን ናት። ደርዊሹ ለሰው ወሬ ደንታ እንደሌለው ገፅታውን አይቶ መመስከር ይቻላል።

Edit with WPS Office

‹‹ወደ ዛውያችን እንኳን በደህና መጣህ›› አልኩት ከአጠገቤ እንዲቀመጥ ጠጋ እያልኩ፡ ለሁሉም ሰላምታ ከሰጠ በኋላ መጥቶ ተቀመጠ፡፡ ክፍሉ ውስጥ የነበሩ ሰዎችን ተራ በተራ አተኩሮ እየተመለከተ በመጨረሻ አይኑ ከዳኛው ላይ ተተክሎ ቀረ፡፡ ሁለቱ ሰዎች ለደቂቃ እርስበእርስ እየተያዩ ቆዩ፡፡ ፍፁም ተቃራኒ ስብእና ስላላቸው ሁለቱ ሰዎች አንዱ ስለሌላኛው ምን ሊያስብ እንደሚችል መገመቴን ማቆም አልቻልኩም፡፡

ትኩስ ፍየል ወተት፣ ጣፋጭ የሾላ ፍሬዎች እና ተምሮችን ለደርዊሹ አቀረብኩለት፡ ሁሉንም አልፈልግም ሲል በትህትና ነገረኝ፡፡ ራሱን አላስተዋወቀንም ነበር፡ ሽምስ ጠብሪዝ እንደሚባልና አምላኩን ፍለጋ ላይና ታች እንደሚማስን ነገረኝ፡፡

‹‹መልካም፡ ታድያ አገኘኸው?›› ብዬ ጠየቅኩት

ራሱን እየነቀነቀ ‹‹ምን ጥርጥር አለው፡ ሁሌም በየቦታው አብሮኝ ነበር›› አለ

ዳኛው በመሃላችን ጣልቃ ገብቶ ‹‹እናንተ ደርዊሾች ህይወትን ለምን እንደዚህ እንደምታከብዷት አይገባኝም፡ አምላክህ ሁሌም ካንተ ጋር ከነበረ ለምንድነው እሱን ፍለጋ ይህን ሁሉ ጊዜ ስትንከራተት የቆየኸው?›› አለው፡፡ ሽምስ በትካዜ ፊቱን አቀጨመ፡ ለትንሽ ጊዜ ራሱን አቀርቅሮ ዝም አለ፡፡ አንገቱን መልሶ ቀና ሲያደርግ ስክን ብሎ በረጋ ድምፅ ‹‹ምክንያቱም እሱ በፍለጋ የሚገኝ አለመሆኑ እውን ቢሆንም፡ ፈላጊዎች ብቻ የሚያገኙት እንደሆነም ይታወቃል›› ብሎ መለሰለት፡፡

‹‹የቃላት ጨዋታ›› ሲል ዳኛው አሾፈ

Edit with WPS Office

‹‹ህይወታችንን ሙሉ አንድ ቦታ ላይ ካሳለፍን አላህን አናገኘውም ማለት ነው? እንደዛ ነው የምትለን? ይህ በፍፁም ተቀባይነት የለውም። ሁሉም ሰው እንዳንተ ቡትቶ ለብሶ ከቦታ ቦታ መንከራተት የለበትም!›› ዳኛው ተናግሮ ሲጨርስ አብረውት የመጡት ጀሌዎቹ በሀሳቡ መስማማታቸውን ለማሳየት ቤቱን በሳቅ ካካታ ረበሹት። ጩኸት፣ በራስ መተማመን የሌለው፣ ደስታ የራቀው ሳቅ ከስልጣን ባለሟሎቹ ሲከታተል መጥፎ ስሜት ወረረኝ። ቃዲውን እና ደርዊሹን ማገናኘት አልነበረብኝም አልኩ ለራሴ።

‹‹አልተረዳችሁኝም፡ አንድ ሰው ከሚኖርበት ከተማ ካልወጣ ፈጣሪውን አያገኝም አላልኩም፡ በእርግጠኝነት ሊያገኘው ይችላል። ወደየትም ቦታ ሳይሄዱ ዓለምን የቃኙ ብዙ ሰዎች አሉ›› ሲል ከቃዲው ሀሳብ ጋር የተስማማ መሰለ

‹‹በትክክል›› አለ ዳኛው የሱ ሙግት ያሸነፈ መስሎት ፊቱ በደስታ እያበራ፡ ደርዊሹ ቀጣይ የተናገረው ግን ደስታውን ቅፅበታዊ አደረገበት ‹‹ክቡር ዳኛ ሆይ፡ እኔ ማለት የፈለግኩት በካባዎች፣ በሐር ጨርቆች እና በውድ ጌጣጌጦች የተከበበ ሰው አላህን ሊያገኘው አይችልም። ልክ ዛሬ አንተ እንደለበስከው ማለት ነው››

ክፍሉ ውስጥ አስፈሪ ዝምታ ነገሰ፡ ሁላችንም ትንፋሻችንን ዋጥ አድርገን ያዝን። ሌላ ይበልጥ አስደንጋጭ ነገር ይከሰት ይሆን እያልን ስንጠባበቅ

‹‹ምላስህ ከደርዊሾችም ይባስ ስል ነው ባክህ›› አለ ዳኛው

‹‹መናገር ያለብኝ ነገር ካለ ዓለም በሙሉ አንገቴን አንቆ ዝም በል ቢለኝ እንኳ ከመናገር ወደኋላ አልልም›› ሽምስ መለሰ። ዳኛው ንግባሩን እንደቋጠረ ነው፡

Edit with WPS Office

ንግግሩ ቢያበሳጨውም እንዲታወቅበት አልፈለገም። ትከሻውን እየሰበቀ ‹ግድ አልሰጠኝም› አይነት ፊት አሳየን።

‹‹መልካም፡ ምንም ይሁን ምን አሁን ስለከተማችን ድምቀት እየተጨዋወትን ሳለ ነው የመጣኸው፡ ብዙ ቦታዎችን እንደጎበኘህ እርግጠኛ ነኝ፡ ከበግዳድ የበለጠ ድንቅ ስፍራ አለ?›› ብሎ ጠየቀው። ሽምስ በእርጋታ ሰዎቹን ተራበተራ ከተመለከተ በኋላ

‹‹በግዳድ ውብ ከተማ እንደሆነች ምንም ጥርጥር የለውም፡ ነገር ግን የትኛውም ውበት ዓለም ላይ ለዘልዓለም አይቆይም። ከተሞች በመንፈሳዊ ምሶሶ ነው የሚቆሙት፡ ልክ እንደ ግዙፍ መስታወት የነዋሪዎቻቸውን ቀልብ ያንፀባርቃሉ። እነዛ ቀልቦች የጠቆሩ፣ ከኢማን የራቁ ከሆኑ ከተሞችም ውበታቸውን ያጣሉ። እንደዚህ ነው የሚሆነው፡ ሁሌም እንደዚህ ነው›› አለ። መስማማቴን ለመግለፅ አንገቴን ከመነቅነቅ በስተቀር ሌላ ምንም አላደረግኩም። ሽምሱል ጠብሪዝ የሀሳብ ጉዞውን ገታ አድርጎ ወደኔ ዞሮ ተመለከተኝ። የብርሃን ብልጭታ የሚፈነጥቁትን አይኖቹን አየሁ፡ ፀሃይ እንደሚሞቅ ልጅ በሰውነቴ ውስጥ ዘልቆ ተሰማኝ። ስሙን ለምን ‹የጠብሪዙ ፀሃይ› እንዳለው አሁን ተረዳሁ፡ ልክ እንደ እሳት ነበልባል ፍንጣቂ ውስጥን እያሞቀ ያነቃል። እውነትም ፀሃይ!

"ብዙ ዱዓዎች ምላሽ ያጡት በተዋቡ ቃላት ነገር ግን መጥፎ ሽታ ካላቸው ብኩል ልቦች ስለሚደረጉ ነው...ቃላቶች እንከን ቢሞሉም ትርጉሙ ልክ ይሁን! እነዚያ እንከን የተሞሉ ቃላት ጌታህ ዘንድ ተወዳጅ ናቸውና" የጠብሪዙ ፀሐይ በመቀጠል ያጫወተንን ታሪክ ላውጋችሁ፦

Edit with WPS Office

‹‹አንድ ቀን ሙሳ ተራራ አካባቢ እየሄደ ሳለ ከርቀት እረኛ ተመለከተ፡ ልጁ በጉልበቱ ተንበርክኮ፣ እጆቹን ወደላይ ዘርግቶ እየፀለየ ነው። ሙሳ የሚፀልይ ሰው በማየቱ ተደሰተ፡ ቀርቦ የእረኛውን ጸሎት ሲያደምጠው ግን የደስታውን ያህል ደነገጠ።

‹‹ጌታዬ፡ ያ አላህ! እከተልህ ዘንድ የት ነው ያለኸው?

ጫማህን ሰፍቼ ፀጉርህን ማበጥርልህ

ልብስህን አጥቤ ተባዮቹን ማጠፋልህ

ንፁሑን ወተት አልቤ የምሰጥህ

ቸር እጆችህን የምስማቸው

ስስ እግሮችህን የምዳብሳቸው

አምላኬ የት ነው ያለኸው?

እንቅልፍ ሰዓትህ ሲደርስ ምቹ አድርጌ ቦታህን የማነጥፈው

ከብቶቼን ሁሉ የምሰዋልህ

ባሰብኩህ ልክ ናፍቶቴና ስስቴ የሚያይለው

አላህ ሆይ የት ነው ያለኸው!›› እያለ ከፈጣሪው ጋር ያወጋል። ሙሳ እነዚህን ንግግሮች ሲሰማ ‹‹በቃህ አቁም›› ብሎ አቋረጠው። ‹‹አንተ መሃይም ይበቃሃል ምን እያደረግክ ነው ለመሆኑ አላህ አንተ እንደገለፅከው ይመስልሃል? አንተ የምታጥበው እግር ያለው ይመስልሃል? ይሄ ፀሎት አይደለም ፈጣሪን መሳደብ ነው›› አለው

Edit with WPS Office

እረኛው በድንጋጤ አፍሮ ይቅርታ ጠየቀ፡ ሌሎች ሰዎች እንደሚፀልዩት እፀልያለሁ ብሎም ቃል ገባ። ሙሳም በትክክል አላህን የሚያመልክበትን ዒባዳ ካስተማረው በኋላ በሰራው ስራ እየተደሰተ መንገዱን ቀጠለ። የዛን ቀን ለሊት ግን ሙሳ የፈጣሪው ድምፅ እንዲህ ሲል ተሰማው ‹‹ሙሳ ሆይ፡ ምንድነው የሰራኸው ያን ምስኪን እረኛ ተቆጥተህ ገሰፅከው፡ ፀሎቱ ምን ያህል ልባዊ እንደሆነ ግን አላስተዋልክም። በተገቢው ልክ እየገለፀኝ አልነበረም ነገር ግን ቅን ነበረ፡ ሃሳቡም ልቡም ንፁህ ነበር። እኔ ወድጄለታለሁ፡ ቃላቶቹ ላንተ ስድብ ቢመስሉም ለኔ ግን ጣፋጭ ነበሩ›› አለው።

ሙሳ የተሳሳተውን ተረዳ፡ በቀጣዩ ቀን ማልዶ እረኛውን ለማግኘት ወደ ተራራው መውጣት ጀመረ፡ እረኛው አሁንም ፀሎት ላይ ነው። ልዩነቱ አሁን በታዘዘው መሰረት ነው እየፈፀመ የነበረው። ከዒባዳ መስፈርቶችና መሰረቶች ላለማጓደል ጥንቃቄ እያበዛ ነው፡ ይንቀጠቀጣል፡ የትናንቱ ደስታና ጉጉት የለም። ሙሳ ለዚህ ሰበብ በመሆኑ አዘነ የእረኛውን ትከሻ መታ መታ አድርጎ ‹‹ጓደኛዬ፡ እኔ ተሳስቻለሁ እባክህ ይቅርታ አድርግልኝ፡ እንደበፊቱ ዒባዳህን እና ዱዓህን ቀጥል። አላህ ዘንድ ይበልጥ የተወደደው እሱ ነው›› አለው። እረኛው ይህን በመስማቱ ተደነቀ፡ ትልቅ እፎይታም አገኘ። ቢሆንም ግን ወደ በፊቱ ፀሎት መመለስ አልፈለገም፡ የተማረውን ሽምድዶ መለፍለፍም አልፈለገም። አሁን ከፈጣሪው አላህ ጋር ግንኙነቱን ማስተካከያ መንገድ አግኝቷል። በየዋህነትና ቅንነት ያደረጋቸውን ፀሎቶች ቢወዳቸውም አሁን ግን ያን ደረጃ አልፏል›› ሲል ሽምስ ታሪኩን ቋጨ።

‹‹አያችሁ ክቡራን፡ ሰዎች ከፈጣሪያቸው ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነት መለካት

Edit with WPS Office

የለብንም››

‹‹ሁሉም ሰው ከአላህ ጋር የሚገናኝበት የየራሱ መንገድ እና ፀሎት ስርአት አለው፡፡ አላህ በቃላቶቻችን አይደለም የሚተሳሰበን፡ እሱ የሚመለከተው ውስጠ-ልቦናችንን ነው፡፡ ለቅቡልነትም ልዩነት የሚፈጥረው ቃላት ማሳመራችን ሳይሆን ልቦናችን የተጥራራ ንፁህ መሆኑ ነው›› ብሎ አስረዳ፡፡

ወደ ዳኛው ተመለከትኩ፡ ፊቱ ላይ አድናቆት፣ መረበሽ፣ ኩራት ይነበባል፡፡ ምንም አስተያየት ሳይሰጥ ነገሩን አድበስብሶ ማለፍ ፈለገ፡ ሰዎች ተጓዡ ደርዊሽ ቃዲውን ተሟገተው ብለው እንዲያወሩ አልፈለገም፡፡ ሁሉም ሰው ከወጣ በኋላ ሽምስን ‹‹ዳኛው የወደደህ አልመሰለኝም›› አልኩት፡፡ ግንባሩ ላይ የተደፋውን ፀጉሩን በእጆቹ ወደኋላ እየገፋ ‹‹ምንም አይደል ሰዎች ብዙ አይወዱኝም፡ ለምጄዋለሁ›› አለኝ፡፡ እኔ ግን በሱ ደስተኛ ነበርኩ

‹‹እንዳንተ ያለ ሰው ወደ በግዳድ ምን ፍለጋ ሊመጣ ቻለ ንገረኝ እስቲ›› አልኩት

የልቤን ናፍቆት... የእድሜዬን ምኞት... መውላዬን ለማግኘት...

"ማፍቀር ወደ አላህ መድረስ ነው"

ሽምስ

ከዘጠኝ ወራት በኋላ...

አንድ ቀን ድንገተኛ ስብሰባ ተጠራን፡፡ ጀማሪና ታላላቅ ተማሪዎች ከሸኻችን እግር ስር ክብ ሰርተን ተቀምጠናል፡፡ ዛሬ ከሆነ ቦታ ደብዳቤ ደርሷቸዋል፡፡

Edit with WPS Office

እንዲህ አሉን

"ከሩቅ ምድር የሚኖር አንድ ዓሊም አለ። አንደበቱ ጣፋጭ ነው። ገጣሚ አይደለም። ዘይቤያዊ ንግግርም አይችልም። በሺዎች ተወዳጅ ተደናቂና ክቡር ነው። ነገር ግን እሱ አፍቃሪ አይደለም። ከ'ኔና ከናንተ እውቀት በራቀ ሚስጥር ከዛውያችን የሆነ ሰው እሱ ዘንድ ሂዶ ጓደኛው መሆን ይኖርበታል። እናም ለዚህ መንፈሳዊ ጉዞ ፍቃደኝነታችሁን ልጠይቅ ነው የሰበሰብኳችሁ"

"አንዳችሁን አዝዤ መላክ እችል ነበር። ነገር ግን ይህ በፍቅር ለፍቅር የሚደረግ ብቻ ነው!" አሉን። ብዙ ተማሪዎች በደስታ ተሞልተው ጉጉት እያፈነደቃቸው እጃቸውን አወጡ። ቆጠርኳቸው፡ ዘጠኝ ነበሩ። እኔም አስረኛ ሆኜ ታዛዥነቴን እጅ በማውጣት ገለፅኩ።

"ከመወሰናችሁ በፊት ግን ልታውቁት የሚገባ አንድ ነገር አለ" አሉን ባባ ሽኽ "ጉዞው አደገኛ ነው፡ ፈተናዎች የሞሉት ከመሆኑም ጋር የመመለስ እድል ላይኖር ይችላል"

በዚህ ጊዜ እጆች ሁሉ ወደ ታች ተመለሱ፡ የእኔ እጅ ብቻ ቀረ።

የመጀመርያ ቀን

ኮንያ የገበያ ማእከል ውስጥ ከጥጥ፣ ስኳርና አታክልት መደብሮች መካከል ትልቅ ጎዳና አለ፡ ጀላሉዲን ሙሐመድ ሩሚ በተማሪዎቻቸው ተከበው ያን መንገድ እያቋረጡ ነበር። ይች ቀን ለመውላና የነፍሳቸውን አጋር ያገኙባት ‹የተባረከች እለት› ናት። መውላና ሩሚ በራሳቸው አንደበት ታሪኩን ያወጉናል

Edit with WPS Office

‹‹በመንገድ ስጓዝ በርካታ ሰዎች ስለሚይዙኝ በቀላሉ አሳብሬ ማለፍ አልችልም፡ የባለጉዳዮች ጥሪ፣ የህፃናት ለቅሶ፣ የነዳያን ልመና ተደምሮ ጉዟችንን ወደ ኋላ ያዘገይብናል። አብዛኞቹ ሰዎች ዱዓ እንዳደርግላቸው ይፈልጋሉ፡ አንዳንዶች ደግሞ እኔን ቀርቦ ማየት ብቻ ይመኛሉ። ከፍ ያለ ተስፋ አንግበው የሚመጡኝ ሰዎችም አሉ፣ አይድንም ከተባለ በሽታ ፈውስ እንድሆናቸው፣ ድግምት እንድፈታላቸው ይጠይቁኛል። እነዚህኞቹ ናቸው የሚያስጨንቁኝ፡ ተዓምር የተሰጠኝ ነብይ፣ ወይም የአላህ ወልይ አይደለሁ እንዴት ይህን ይጠይቁኛል!

ከገበያው መሃል እያቋረጥን ስኳር መደብሩ ጋር ስንደርስ ተጓዡ ደርዊሽ የህዝብ ማእበሉን እየገፋ ወደኔ ሲመጣ ተመለከትኩ፡ ቀልጠፍ ብሎ በተመጠነ እርምጃ ሲራመድ፣ አይኖቹ ውስጤን ሰርስረው ሲመለከቱ ይታየኛል። ተጓዥ ደርዊሾች አላህን ፍለጋ ከቦታ ቦታ በሚዘዋወሩበት ጊዜ ለብዙ አመታት ኮንያ መጥተው አይቻቸዋለሁ። ፀጉራቸውን አይቆረጡም ወይም እስከነጭራሹ አያሳድጉም፡ አለባበሳቸውም ሆነ ስራዎቻቸው ከተለመዱ ሰዎች ወጣ ያለ ነው። እናም ይህን ደርዊሽ ለመጀመርያ ጊዜ ሳየው ያስደነገጠኝ ውጫዊ ገፅታው ሳይሆን አይኑ ነበር። እይታው ከጊሌ በላይ ያሳምማል። ጎዳናው መሃል ላይ ቆሞ እጆቹን ወደላይ ከፍ አደረገ፡ የሰዎችን ግርግር ብቻ ሳይሆን የጊዜ ዑደትን ማስቆም የፈለገ ይመስላል። በድንገት ድንጋጤ መላ ሰውነቴን ወረረኝ፡ ፈረሴም በፍርሃት ማሽካካት፣ ጭንቅላቱን ወደ ላይ ወደ ታች እያወዛወዘ መቅበጥበጥ ጀመረ። ላረጋጋው ሞከርኩ ነገር ግን እኔንም ፍርሃት ስለያዘኝ አልቻልኩም።

Edit with WPS Office

ደርዊሹ ከሚንቆራጠጠው ፈረሴ አጠገብ ደረሰ፡ ጆሮው ጋር ጠጋ ብሎ አንዳች ነገር ሲያንሾካሹክለት እንስሳው ትንፋሹ ይቆራረጥ ጀመር፡ እንደ መሰናበቻ ምልክት እጁን ስያወዛውዝለት ደግሞ ፈረሱ ፍፁም ተረጋጋ። በቦታው የነበሩ ሰዎች በሙሉ ሁኔታውን አይተው ተደንቀዋል፡ ‹‹ይህማ አስማት ነው›› የሚሉ ድምፆች ይሰሙኛል።

‹‹የምስራቅና የምዕራብ ምሁር የሆንክ ታላቁ ዓሊም ሆይ፡ ስላንተ ብዙ ሰምቻለሁ። ጥያቄ ልጠይቅህ ነው የመጣሁት ይቻላል?›› አለኝ

‹‹ይቻላል፡ ጠይቅ›› አልኩት

‹‹መልካም፡ በመጀመርያ ግን ከፈረስህ ላይ ወርደህ ከኔ እኩል መሬት ላይ መቆም አለብህ›› አለኝ። መናገር እስኪያቅተኝ ድረስ በሁኔታው ተገረምኩ፡ አብረውኝ የነበሩ ሰዎችም በንግግሩ ተደናግጠዋል፡ ማንም ሰው በዚህ መልኩ አናግሮኝ አያውቅም ነበር። ተናደድኩ፣ በቁጣ ሆዴ ሲቃጠል ፊቴ ሲቀላ ታወቀኝ። ነገር ግን ኩራቴን ዋጥ አድርጌ ከፈረሴ ላይ ወረድኩ። ደርዊሹ ፊቱን አዙሮ ጥሎኝ ሄደ።

‹‹ቆይ እንጂ ወዴት ትሄዳለህ›› ብዬ ጠራሁት ተከትዬ ያዝኩትና ‹‹ጥያቄህን መስማት እፈልጋለሁ›› አልኩት። ተመልሶ ዞረ፡ ለመጀመርያ ጊዜ ፈገግ ሲልም አየሁት

‹‹እሺ እባክህን ንግረኝ...›› ብሎ ጥያቄውን ጀመረ። ‹‹ከነብዩ ሙሐመድ ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እና ከሱፊው ቢስጣሚ ማን ይበልጣል?›› አለኝ

‹‹ምን አይነት ጥያቄ ነው ይሄ!›› ብዬ ጮህኩ ገና እንደሰማሁት፡ ‹‹የአላህ

Edit with WPS Office

ሰላምና ደህንነት በሳቸው ላይ ይስፈንና የተከበሩትን ውድ ነብይ፣ የመልእክተኞችን መደምደሚያ እንዴት ከተራ ሱፊይ ጋር ታወዳድራለህ?›› አልኩት። በርካታ ሰዎች በጉጉት ተሞልተው ከበቡን፡ ደርዊሹ ግን ለግርግሩ ትኩረት ሳይሰጥ ዝም ብሎ ፊት ፊቴን እየተመለከተ ያጠናኛል። ‹‹እባክህን እስቲ አስብ የአላህ መልእክተኛ ‹አላህ ሆይ፡ ተገቢውን ማወቅ አላወቅኩህም ይቅር በለኝ› አላሉም? ቢስጣሚ ደግሞ ‹የተቀደስኩ ነኝ ፈጣሪዬ እኔ ውስጥ አለ› ብሎ አልተናገረም? አንድኛቸው ከፈጣሪው ጋር ባለው ግንኙነት ተናንሶ ሌላኛቸው ደግሞ ፈጣሪዬ እኔ ውስጥ ነው ካለ ማነ ነው የሚበልጠው?›› አለኝ

ልቤ ከጉሮሮዬ አልፋ ልትወጣ ቀረበች፡ ጥያቄው የሞኝ ጥያቄ አይደለም፡ ሽፋኑ ሲገለጥ አስቸጋሪ እንቆቅልሽ እንደሆነ ገባኝ። እንደ ንፋስ ሽውታ ለስለስ ያለ ፈገግታ ከደርዊሹ ከንፈር ለአፍታ ታየ። አሁን ይህ ሰው ዝም ብሎ እብድ እንዳልሆነ ተረድቻለሁ። ጠያቂ ነው፤ ከዚህ በፊት አስቤው የማላውቀውን ጥያቄ የጠየቀኝ ሰው።

"ምን ለማለት እንደፈለግክ ገብቶኛል" ብዬ ጀመርኩ የሚንቀጠቀጠውን ድምፄን ለመደበቅ ጉሮሮዬን እየጠረግኩ። "ሁለቱን ንግግሮች አነፃፅሬ አስረዳሃለው፡ የቢስጣሚ ንግግር ላቅ ያለ ቢመስልም ነገሩ ግን የተገላቢጦሽ ነው" አልኩት

"እሺ እያዳመጥኩ ነው" አለኝ

"አየህ፡ የአላህ ፍቅር ወሰን የሌለው ውቅያኖስ ነው፡ የሰው ልጆች ከውሃው በቻሉት መጠን ለመቅዳት ይሞክራሉ። ነገር ግን በስተመጨረሻ እያንዳንዳችን የምናገኘው የውሃ መጠን በያዝነው እቃ ልክ ይወሰናል። አንዳንዶች በርሜል፣

Edit with WPS Office

ሌሎች ባልዲ፣ እንዲሁም ከፊሎች ደግሞ ኩባያ ብቻ ይኖራቸዋል"

እየተናገርኩ ሳለሁ የደርዊሹ ፊት ሲለዋወጥ ተመለከትኩ፡ ከስስ ፈገግታ ለንግግሬ እውቅናን ወደ መቸር፣ ከዚያ የራሱን ሀሳብ በሌላ ሰው ቃላት እንዳገኘ ሰው ደስታ አየሁበት። መልስ መስጠቴን ቀጥያለሁ

"የቢስጣሚ እቃ ከነብዩ ጋር ሲወዳደር ትንሽ ነው፡ በያዛት እቃ ሞልቶና ጥሙን ቆርጦ በነበረበት ደረጃ ደስተኛ ሆነ። አላህን ከውስጡ ማግኘቱ ግሩም ነው፤ ነገር ግን ከዛ በኋላም በርሱና በአላህ መካከል ልይ መሆን አለ። አንድ መሆን አይገኝም። ወደ ፍጥረታት አለቃ ስንመጣ በአላህ የተመረጡ፣ የሚሞሉት ከማንም የበለጠ ትልቅ እቃ ያላቸው ናቸው። ለዚህም ነው አላህ በቁርአኑ "ልብህን ለአንተ አላሰፋንልህምን? (አስፍተንልሃል)" ያላቸው፡ ልባቸው ሰፊ፣ እቃቸው ግዙፍ ነውና አይረኩም፡ በጠጡ ቁጥር በጥማት ላይ ጥማት ነው የሚጨምርላቸው። ከማንም በላይ አላህን ያውቃሉ ግን ተገቢውን ያህል አላወቅኩህም ያስባላቸው ይኸው የእቃቸው ስፋት ነው"

ደርዊሹ ተደሰተ፤ ከጭንቅላቱ ዝቅ ብሎ አመሰገነኝ። እጁን ደረቱ ላይ አሳርፎ ለአላህ ምስጋና እያደረሰ ለደቂቃዎች ቆየ። ቀና ሲል ዳግመኛ አይኖቻችን ተጋጩ፡ ቅድም ያላስተዋልኩትን ብልህነት አሁን ከአይኖቹ መመልከት ቻልኩ። የደራረቁ ቅጠሎች ከእግሮቻችን ስር ይሸከረከራሉ፡ ደርዊሹ በምትጠልቀው ፀሃይ ውስጥ እየሞተች ባለች ብርሃን ይመለከተኛል፡ በክብር ዝቅ አለልኝ፤ እኔም በተመሳሳይ ለክብሩ አጎነበስኩ። በዚህ ሁኔታ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየን አላስታውስም። ፀሃይዋ ከአናታችን ላይ ሐምራዊ መሆን ጀምራለች። ጊዜ እያለፈ፣ እየመሸ ሲሄድ በዙርያችን ያሉ ሰዎች በፍርሃት ይዋከቡ ጀመር።

Edit with WPS Office

ከዚህ በፊት ለማንም ሳጎነብስ አይተውኝ አያውቁም ነበር፡ አሁንም 'ተራ ተጓዥ' ለሚባል ሱፍይ ይህን ክብር መቸሬ ሰዎችን አስደንግጧል። የቅርብ ተማሪዎቼንም ጭምር

ደርዊሹ ይህን ስሜት ተረድቶት ነው መሰል በዝግታ እንደማንሾካሾክ ያህል "አሁን ለአድናቂዎችህ ትቼህ መሄዴ ነው" አለኝ

"እዚሁ ቆይ" ብዬ ተቃወምኩት "እባክህን አትሂድ እዚሁ ሁን"

ጥልቅ ሀሳብ ውስጥ ሲገባ ተመለከትኩ፡ መናገር እየፈለገ እንዳቃተው፣ ወይም እንዳልቻለ ከንፈሮቹን ማዘዝ ተሳነው። በዛች ቅፅበት በዛ ሁኔታ ያልጠየቀኝ ጥያቄ ተሰማኝ

"እና አንተስ ታላቁ መምህር፡ ንገረኝ እስቲ ያንተ እቃ ምን ያህል ትልቅ ነው?"

የዛኔ ምንም ንግግር የለም፡ ከቃላቶች ዓለም ወጣን፡ ወደ ደርዊሹ አንድ እርምጃ ተቃረብኩ ከጥቋቁር አይኖቹ ውስጥ የወርቅ ስብርባሪዎችን ማየት እስኪያስችለኝ ድረስ ተጠጋሁት። በድንገት ግን ይህንን ጊዜ ከዚህ በፊት ኖሬው ያሳለፍኩት ይመስል እንደ ትዝታ ታወሰኝ። አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ለበርካታ ጊዜያት አብረን ያሳለፍን ያህል ጥቃቅን ጉዳዮችን ማስታወስ ጀመርኩ። ረጅም፣ ቀጭን፣ ፊቱን በፀጉሩ የሚሸፍን ሰው፣ ጣቶቹ......አዎ አወቅኩት፡ ከፊት ለፊቴ የቆመው ደርዊሽ ሁልጊዜ በህልሜ ሳየው የነበረው ሰው ነው።

"ያለ ሸኽ የሚጓዝ ሰው ለሁለት ቀናት መንገድ ሁለት መቶ ዓመታት ይፈጃል"

የመውላና ሩሚ እና ሸምስ ግንኙነት ስለሚጀምርበት ክስተት አራት ዓይነት

Edit with WPS Office

ዘገባዎች አሉ። አንዱ ከኤሊፍ ሸፈቅ 40 rules of love የተወሰደ ከላይ ያነሳነው ሲሆን ቀሪዎቹ ሶስት ታሪኮች ደግሞ እንደሚከተለው ተሰንደዋል።

አንድ፦ ከባህር ዳርቻ ቁመው እያወጉ ነው፤ ጀላሉዲን ሩሚ በእጃቸው አንድ ኪታብ (መፅሀፍ) ይዘዋል። የልቡ ሰው ሸምሱዲን ከእጃቸው ኪታቡን ነጥቀው ከባህሩ ወረወሩት። ቅጂ የሌለው መፅሓፋቸውን ከባሕር ሲወረውሩባቸው ሩሚ ተቆጡ። እያፈጠጡበት፦‹‹ምን ሁነሃል? እውቀት እኮ ነው የጣልከው! አቻ የሌለውን መፅሐፍ እንዴት ውሃ ውስጥ ትጥልብኛለህ?›› ብለው ያዙት።

ሸምስ የሩሚ ድንፋታ ብዙም ግድ ሳይሰጣቸው ወደ ባሕሩ እየተመለከቱ፦‹‹ኪታቡን ትፈልገው ነበር እንዴ?›› አሉት። ሩሚ ንዴቱ ባሰባቸው፦‹‹እንዴት አልፈልገውም?›› ሲሉ በጥያቄው ተገርመው፣ በስራቸው ተናደው የሚያደርጉት ጠፋቸው። ሸምስ ወደ ባሕሩ ጠጋ ብለው የወረወሩትን ኪታብ ያለ አንዳች እርጥበት ከባሕሩ አውጥተው ለሩሚ አቀበሉ።

ሩሚ የሚያዩትን ማመን ተስኗቸው ፈዘዙ። ሸምስም፦‹‹ውሃ የሚያበላሸውን ሳይሆን ልብህ ሸምድዶ የሚያፀናውን ዕውቀት ቅሰም›› ብለው ምክር ብጤ ሰጡ። ሩሚ እየተደመሙ፦‹‹እባክህ ተማሪህ ሆኜ ልከተልህ!›› ብለው ተማፀኗቸው።

ሁለት፦ የመውላና መድረሳ ውስጥ ነው፡ እንደተለመደው ተማሪዎች ከፊት ለፊት እግራቸው ስር ተቀምጠው ልዩ ልዩ ደርሶችን ይማራሉ። በርከት ያሉ መፃሕፍት ተደርድረዋል። አንድ እንግዳ ሰው ሳይጋበዝ በቀጥታ ወደ'ሳቸው ተጠግቶ ጥግ ላይ ተቀመጠ። ጥቂት እንደቆየም ወደ ተከመሩት መፃሕፍት እየጠቆመ "እነዚህ ምንድን ናቸው?" ብሎ ጠየቀ። ሩሚ በዚህ ድንገተኛ ጣልቃ

Edit with WPS Office

ገብነት የተደሰቱ አይመስሉም። በእንግዳው አላግባብ ድፍረት ተገርመዋል። ከመሆኑም ጋር ስሜታቸውን ቆንጥጠውና ቁጣቸውን ዋጥ አድርገው "አንተ መረዳት ከምትችለው በላይ ነው" ብለው መለሱለት። ሩሚ ይህን ንግግር ከመናገራቸው አፍታም አልቆየ የተደረደሩት መፃሕፍት በእሳት ተያያዙ። በቦታው የነበሩ ጠቅላላ ሰዎች ተደናገራቸው። ሩሚ በድንጋጤ ተሞልተው "ይህ ምንድነው?" አሉ። "ይህ አንተ መረዳት ከምትችለው በላይ ነው" ሽምስ የሩሚን ቃል ተጠቅመው መለሱና ከስፍራው ገለል አሉ። በሁኔታው የተደነቁት ሩሚ ማስተማራቸውን ትተው እንግዳውን ፍለጋ ወጡ።

ሶስት፦ ሽምስ ለረጅም ጊዜ የሩሕ ወዳጅ ሲፈልጉ ቆይተዋል። ሸይኽ ሩክኑዲን ኮንያ ቢሄዱ እዚያ ፍለጋው እንደሚያበቃ ነገሯቸው። ኮንያ ትንሽዬ ሆቴል ውስጥ እያሉ አንድ እለት ሩሚ በተማሪዎችና አድናቂዎች ተከበው በዚያች ሆቴል በኩል ሲያልፉ ሽምሱዲን አይተው አስቆሟቸው።

"እውቀት/መማር ፋኢዳው ምንድነው?" የሚል ድንገተኛ ጥያቄ አስከተሉ

"የአላህን መልእክተኛ ለመከተል እና እሳቸው ዘንድ መዳረሻ መንገድ ነው" ብለው ሩሚ መለሱ

"አጥጋቢ ምላሽ አይደለም" አሉ ሽምስ፡ ሩሚም "መልካም! አንተ ንገረኛ መልሱን። እውቀት ዓላማው ምንድን ነው?"

"እውቀት፣ ጥበብና ትምህርት ዓላማቸው ወደ መነሻ ምንጬ ማድረስ ነው። እውቀት እና ጥበብ ወደ መነሻው የማያደርስህ ከሆነ ካገኘኸው እውቀት መሀይምነት የተሻለ ነው"

Edit with WPS Office

ሩሚ በሸምስ አስተውሎትና ንግግር እጅግ ተማረኩ። ወዲያውኑም የእሳቸው ተከታይ ለመሆን ወሰኑ።

ከእውቀት ወሰን ያላዳረሱት ጠረፍ አልነበረም። ነገር ግን ሩሚ እርካታን ማግኘት አልቻሉም። ዘውትር 'አብዳል' ፍለጋ ይማስኑ ነበር። ልባቸው ላይ የሚገኝን ሽንቁር መንጭቆ የሚያወጣላቸው፣ ክፍተታቸውን የሚሞላና 'ሐቅ'ን የሚገልጥላቸው መሪ ይሹ ነበር። የሩሚ በኩር ልጅ ሻህ ወለድ "የሸምስን ልቅና የተረዳ ማንም የለም" ሲል ይሞግታል። "ሸምስ ራሳቸውን ረስተው ወደ አላህ ከተጠቀለሉና ማንነታቸውን በአላህ ካከሰሙ ጥቂት ሰዎች መካከል ተጠቃሽ ናቸው። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ኑረታቸው ነፍስ በአካል ውስጥ ያላትን ቦታ ይመስላል። ነፍስ በአካል ውስጥ ስትኖር በዓይን አትታይም። ሸምስን የመሰሉ ብጹኣንም በማሕበረሰቡ እይታ ውስጥ ሳይገቡ ይኖራሉ። አላህ ከሰዎች እውቅና ደብቆና ሸሽጎ ያቆየው ለሩሚ ታማኝነትና የፍቅር ምርኮኝነት ሽልማት ሊያደርገው ነው። ዋጋውን ያወቀው ሩሚ ብቻ ነው"

ከሸምስ ጋር በነበራቸው ቆይታ ሩሚ ልባቸው ውስጥ የነበረው ቅሬታ በሙሉ ተነነ። ለረጅም ዓመታት ሲያስጨንቋቸው የነበሩ ጥያቄዎች ተመለሱላቸው። ክፍት የነበረው ጡብ በሸምስ ተሞላላቸው። ራሳቸው ዓለማዊ ከተባሉ ነገሮች በሙሉ አግልለው መነኑ። ሌሎች የማይገነዘቡትን መረዳት ለሌሎች የማይሰማን ማድመጥ ጀመሩ። ከሸምስ ጋር ቁጥርን ፍቀው በሩሕ መጥቀው አንድ ሆኑ። በሁለት የተለያየ አካል ውስጥ የሚገኝ አንድ ነፍስ። ወደ ቤታቸው ወሰዷቸውና እንዲህ አሉ

"...ቤቴ ላንተ ምቹ መኖርያ ባይሆንም እባክህ እዚሁ ቆይና ውለታ ዋልልኝ።

Edit with WPS Office

ዛሬ ያፈራሁትን ንብረት ወደፊትም የማገኘውን ሀብት በሙሉ ከፊትህ የማኖር ታዛዥ ባርያህ ነኝ"

ከዚህ በኋላ ሸምስና ሩሚ ነፍሳቸውን አንድ አደረጉ፡ ፍቅር ሩሐቸውን አጣምሮ አንዱ ለሌላው ምላኤነትን አላበሰ። አርባ ቀናት ሙሉ ሌቱንም ቀኑንም ከአንድ ክፍል ሳይወጡ ስለ ፍቅር አወሩ፡ ተመጋገቡም። ሸምስ ቅንጣት ሳይሰስቱ የተሰጣቸውን ሁሉ ለሩሚ አፈሰሱ። ሩሚም ሸምስን ካገኙ በኋላ የቀድሞ ማንነታቸው ርቆ በረረ፡ የከተማዋ አንጋፋ ኢማምነታቸውን መምህርነታቸውን ተዉ። ሰዎች እጅግ በጣም ይወዷቸው ስለነበር የሩሚ ‹‹መቀየር›› አበሳጭቷቸዋል።

በአሉባልታ የማይወላገድ፣ ፅኑ ፍቅር ነበራቸው። ሩሓቸው በአዘልይ የሙሓባ ገመድ የተገመደ የማይነጣጠል አብሮነትን ታድሏል። ደረሳው ጀላሉዲን ሩሚ እና ሙረቢው ሸምስ አል ጠብሪዝ።

ከዕለታት በአዱ ቀን የወዳጅነታቸውን ገመድ ለመበጠስ የዳዳ አንድ ግለሰብ፣ ወደ ጀላሉዲን አል—ሩሚ ቀረበ።

«ያንተ ሼኽ ሸምስ ጠብሪዝ፣ አስካሪ መጠጥ ሲጠጣ አይቼዋለሁ!» በማለት ወሬ አቀበለ። ሩሚ በልበ ሙሉነት የታጀበ ምላሻቸውን ሰጡ

«ነፍሴ በእጁ በሆነችው አላህ እምላለሁ። የኔ ሸምስ! ልብሳቸው በመጠጥ ተጨማልቆ ባየው ከሰውነታቸው ላይ የኸምር ሽታ ቢሸተኝ እንኳ፣ ሌላ ሰው ደፍቶባቸው ነው እላለሁ። ደግሞ፣ ከተራራ አናት ወጥተው ቢቆሙ እና «አነ ረቡኩሙል አዕላ!»እያሉ ብሰማ ቁርኣኑ ውስጥ ያለውን አያት እያነበነቡ ነው

Edit with WPS Office

ብዬ ነው የምናገረው። በሙሉ ልቤ!

አንተም ከአጠገቤ ጥፋ! እኔ ሸምስን የማውቃቸው፣ የማያቸው በዓይኔ አይደለም። በሩሔ ነው!»

የሩሚ ምላሽ ያስደነገጠው ቧልተኛም ሀፍረትን ተከናንቦ ወደ መጣበት ተመለሰ!

በድርቅ የተመታ ሌጣ መሬት ላይ ዝናብ ሲዘንብ ወደ ለምለምነት እንደሚቀየረው ያህል ነው የሁለቱ ሰዎች ግንኙነት ሃለታቸውን የቀየረው። ሩሚ ለዘመናት ሳይረሱ ያነገሳቸው ከሸምስ ጋር በነበራቸው ቆይታ ያገኙት ነገር ነው። ብዙዎች ከሸኻቸውና ሙረቢያቸው ጋር በሚኖራቸው ቆይታ ከፍታን ይዘልቃሉ። እንደ ሸምስ እና ሩሚ ግን በአንድ ቀን እይታ የተዋሀደ የለም። አሁን ሩሚ እና ሸምስ በአንድ ጣርያ ስር መኖር ጀምረዋል። ሩሚ ማስተማራቸውን ሆነ ሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት ካቆሙ ጥቂት የማይባሉ ጊዜያት አልፈዋል። ሁሉን ትተው ወደ ሸምስ ተጠጉ። በአጭር ጊዜያት ውስጥ በተፈጠሩት ክስተቶች የሩሚ "መለወጥ" በተማሪዎቻቸው፣ ተከታዮቻቸውና ቤተሰቦቻቸው ልቦና ውስጥ ቅሬታ ፈጠረ። ሺዎች የሚወዱትና የሚናፍቁት ትምህርታቸው ተቋረጠ...

የሩሚ ተማሪዎች ሸምስን ከኮንያ የሚያስወጡበት መንገድ ሲፈልጉ ዘዴ ሲያሰላስሉ ቆዩ። ይህ ቂምና ጥላቻ ስር ሳይሰድ በፊት ሸምስ ኮንያን ለመልቀቅ ወስነው የነበረ ቢሆንም ሩሚ በፍፁም አይሆንም ሲሉ ሞግተውና ለምነው አስቀሯቸው። ነገር ግን ሸምስ መቋቋም ከሚችሉት በላይ ሲሆን የወዳጃቸውን ተማፅኖ ረግጠው አለፉ። በ1246 ወደ ሶሪያ አቀኑ። ከሩሚ ጋር የነበራቸው

Edit with WPS Office

ቆይታ 18 ወራትን ብቻ የዘለቀ ሆነ።

የሸምስ መጥፋት ያስደነገጣቸው ሩሚ ራሳቸውን ከውሃ ውስጥ እንደወጣች ዓሳ ነበር የመሰሉት። ሸምስም አንዳች አድራሻ ሳያስቀምጡ፡ የሄዱበትን አቅጣጫ ሳይጠቁሙ ነበር የሄዱት። ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላ ከደማስቆ አንድ ደብዳቤ መጣ። ለዚያ ምላሽ ሩሚ እጅግ ብዙ የናፍቆት ተማፅኖዎችን ቢልኩም ዳግም ምላሽ ማግኘት አልቻሉም ። ሸምስ ደብዛቸው ጠፋ። ቀናት ባለፉ ቁጥር ሩሚ ጭንቀት ውስጥ ገቡ፡ ጊዜ በረዘመ ሂደት ብቸኝነትን እየመረጡ፣ ከሰዎች እየተገለሉ፣ ቃላት ከአንደበታቸው እስኪናፈቅ ድረስ ዝምታ እያበዙ መጡ። ይህ የሩሚ ጭንቀት ያሳሰባቸው ተማሪዎች በእነሱ ምክንያት መምህራቸው የገቡበት ሁኔታ አሳዘናቸው። ሸምስን መፈለግ የእነሱ ተራ ሆነ። ፍቃደኛ ሆነው ቢመጡ ላያስቸግሯቸውና ጠላት ላይሆኑባቸው መውላና ሩሚ ፊት ምለው ተገዘቱ። ይቅርታ ጠይቀውም ሱልጣን ወለድ ሸምስን ከገቡበት ገብቶ ያመጣቸው ዘንድ ላኩት።

ሩሚ 'ሸምስ ላይመለስ ይችላል' የሚል የአፍቃሪ ስጋት ውስጣቸውን ይበላዋል። በሕይወታቸው አላህ ከዋለላቸው ትልቁ ጸጋ መካከል ከሸምስ ጋር የነበራቸው ጓደኝነት ነው። ዳግመኛ እሱን ማጣት አይፈልጉም። የሚከፈለውን መስዋእትነት ሁሉ ከፍለው ሸምስን መመለስ ወስነዋል። በአንድ በኩል አላገኘው ይሆናል የሚል ስጋት ሲገዘግዛቸው ምኞታቸው እንዲሰምር የሚያደርጉት ተስፋ ደግሞ ሲያለመልማቸው ሻህ ወለድ የተሰጠውን ተልእኮ አሳክቶ ተመለሰ። እንደ ጥላቸው ከጎናቸው ሳይለይ እንደ ውድ ንብረት ዓይኑን ከላያቸው ሳይነቅል አምጥቶ ሸምስን ለሩሚ አስረከበ።በውሃ እጦት ሲሰቃይ የነበረው ዓሳ ዳግመኛ ውሃ ውስጥ ሲዘፈቅ ሕይወት ዘራ። ሩሚም የሕይወት አዛዡ፣ መሪውና የብጹእነት አርአያው ሸምስ መሆናቸውን

Edit with WPS Office

በግልፅ አወጁ።

"ከፍ ብለህ ለመብረር ጭነትህን ቀንስ"

ሸምስና ሩሚ የተርቢያ መንገድ

ሸምሱ-ጠብሪዝ ጀላሉዲን-ሩሚን በጣም ከባድ በሆነ የሩሕ ተርቢያ ውስጥ እንዲያልፉ አድርገው ነበር። አንድ ምሽት መውላና ጀላሉዲን ሙሐመድ ሩሚ ሸምስን ቤታቸው ጋበዙት፡ የሩሚ መምህርና መሪ የሆኑት ሸምስ ግብዣውን ተቀብለው ሄዱ። መውላና ቤት ደርሰው ሲገቡ ምግቡ ተዘጋጅቶ ሱፍራው ሞልቶ አዩ፡ ደስም አላቸው። ነገር ግን አንድ ነገር ጎድሏል

"እባክህን ወይን አምጣልኝ" ሸምስ ያልተጠበቀ ጥያቄ ሰነዘሩ። ሩሚ በድንጋጤ ፈዝዘው ቀሩ፡ ጥቂት ቆይተውም "ምን አልከኝ ወይን?" የሰማሁት ልክ ነው ወይስ ከየት የመጣ ድምፅ? ተጠራጥረው ጠየቁ

"አዎ ወይን ጠጅ መጠጣት እፈልጋለሁ" ብለው ሸምስ አረጋገጡ

"በዚህ ምሽት ወይን ከየት አገኛለሁ?" መውላና ለመሸሽ ሞከሩ

"የከተማዋ ነዋሪዎች በሙሉ ያውቁኛል እኮ፡ እኔ እንዴት መጠጥ ልገዛ እሄዳለሁ?" ነገሩ እንዳይሳካ ምክንያት መደርደር ጀመሩ

"ተማሪዬ መሆን ከፈለግክ፡ ያዘዝኩህን በሙሉ መፈፀም አለብህ። ዛሬ ወይን ካላመጣህልኝ ምግብህን አልበላም፣ አልናገርም ለሊቱን መተኛትም አልችልም" አሉ።

ሸምስን እጅግ ይወዱት ነበር፡ የፍቅርን ጥልቀት ያስተማራቸው፣ ሁልጊዜ

Edit with WPS Office

የጎደላቸውው አንዳች ነገር እንዳለ ሲሰማቸውና ያን ጉድለት የሚሞላላቸው ሰው ሲፈልጉ ከርመው አላህ ከሸምስ ጋር አገናኛቸው። ክብራቸውን፣ ዝናቸውን፣ ተማሪዎቻቸውን፣ ጠቅላላ ሀብትና እና ማንነታቸውን ጨምረው ለሸምስ አሳልፈው ሰጥተዋል። ሩሚ ረጅሙን ካባ ለብሰው ወደ መጠጥ ቤት ሊሄዱ ተነሱ። ጠርሙስ ከውስጥ ደብቀው በብዛት ክርስትያኖች ወደሚገኙበት መንደር ማቅናት ጀመሩ።

ከዝች ቀን በፊት ማንም ሰው ሩሚ ላይ መጥፎ ጥርጣሬ አሳድሮ አያውቅም ነበር። ነገር ግን ያን ቀን እዛች ስፍራ ሰዎች ሲያዩዋቸው ደነገጡ። 'ይህ ታላቅ ሰው እዚህ ምን ይሰራል?' ብለው ከኋላ ኋላ ቀስ እያሉ ይከታተሏቸው ጀመር።

የተወሰኑት 'ሰውየው አበደ!' ሌሎች ደግሞ 'ይህን ሙናፊቅ አላህ አጋለጠው!' አንዳንዶቹ 'የሰውየው እውነተኛ ማንነት ይህ ነው' እያሉ ፈረዱ። ወደ ሙረቢያቸው ሸምስ ኸምሩን በእቃ እንደተሸከሙ በውርደት ዝቅ ብለው ሀፍረት ተጭኗቸው ተመለሱ።

"ከዚህስ በኋላ ምንድን አለ?" ብለው ሸምስን ጠየቁ። ጠብሪዝም አሉት :-

"ይበቃል! ይህን ኸምር ወዲያ ጣልና ልብስህን እጠብ እራስህንም አፅዳ... ጀላሉዲን ሆይ ስማ– አንተ አሁን ልክ እንደ ትንሽዬ ቡቃያ ነህ፤ የጥምጣምህ ጉራ (መታበይ) አናትህ ላይ ትልቅ ቋጥኝ ሆኖ ነበር። ወደ እውነተኛ ማንነትህ፡ ያለ ምንም ቅፅልና ማዕረግ እንድትመለስ ነው ያገዝኩህ። ሩሕህን ከሚያደፈርሳት ነገር መንጭቀህ ወደ ራስህ ተፈጥሯዊ ማንነት ትመለስ ዘንድ ሻትኩ። እራሳቸውን በሰዎች ዓይን ቅዱስ ለማድረግ የኃይማኖት ሰዎች ከፈበረኩት ግርማ እንድትርቅ፣ ይህን ኩራት ካንተ ማስወገድ ፈለግሁ፤ እናም ይኸው ያን ቋጥኝ ሰብሬልሃለሁ!"

Edit with WPS Office

"አላህ ዘንድ ካንተ የተሻለ በወንጀሉ የሚፀፀት ስንት አለና፤ በእውቀትህ ወይ በአምልኮህ እንዳትታበይ፤ ነፍስህንም ሰዎች ላይ አታጥራ!"

እነዚህን በመሳሰሉ ተርታ ሰዎች ሊረዷቸው በማይችሉ ሁኔታዎች የሩሚ ተማሪዎች ዳግም ጥላቻና ፍርሀት አገረሸባቸው። የመምህራቸው ስም ሳይጎድፍ የነበራቸው ዝና ሳይበላሽ በፊት አንዳች መፍትሄ መፈለግ እንዳለባቸው ተማከሩ። ከዚህ በፊት የገቡትን ቃልኪዳን ዘነጉ፡ ሽምስን ለማስወገድ ሴራ ጎነጎኑ። የተንኮሉ ዋና ተዋናይ የጀላሉዲን ሩሚ ልጅ ዓላኡዲን ነበር የሚል መላምት አለ። መላምቱን የሚያጠናክር እውነት ደግሞ ይኸው ልጅ በሞተ ጊዜ ሩሚ ሰላተል ጀናዛ ለመስገድ ፍቃደኛ አለመሆናቸው ነው። ሩሚ እና ሽምስ ከኸልዋቸው ውስጥ እየተወያዩ ሳለ ገዳዮቹ ሽምስን ጎትተው አወጡና ወግተው ገደሏቸው ይባላል። ሰባት ሰዎች ነበሩ፡ ከገደሏቸው በኋላ ሬሳቸውን ወስደው የውሃ ጉድጓድ ውስጥ መጨመራቸው ይነገራል።

በሌላ ዘገባ ደግሞ ገዳዩ ጩቤውን መዝዞ ከሽምስ ልብ ውስጥ ሲሰነቅረው ሽምስ በነጎድጓዳማ ድምፀት አንዳች ነገር ተናገሩ። በዚህ ጊዜ ሁሉም ሴረኞች ራሳቸውን ስተው ወደቁ። ነቅተው ወደ ዓቅላቸው ሲመለሱ ሽምስ በአካባቢው የሉም። መሬት ላይ ግን እንጥብጣቢ ደም ይታይ ነበር። እውነታው ያም ሆነ ይህ መውላና ሩሚ ለሁለተኛ ጊዜ ወዳጃቸውን አጡ። ነገር ግን ዳግም መገናኘት የተስፋን ገመድ አልበጠሱም። ከተለያዩ ቦታዎች ወደ ኮንያ ይመጡ የነበሩ መንገደኞችን ነጋዴዎችን በሙሉ ስለ ሽምስ ያጠያይቃሉ። ብዙዎች ሩሚን ለማረጋጋት ሲሉ ያልተፈጠረን ታሪክ ይነግሯቸዋል። የሩሚ ልብም በደስታ ሀሴት ትሞላለች።

አንድ ቀን የሆነ መንገደኛ ከሶሪያ መምጣቱን እና ሽምስን ደማስቆ ውስጥ

Edit with WPS Office

መመልከቱን ነገራቸው። ይህን አስደሳች ብስራት የሰሙት ሩሚ በደስታ እየተፍነከነኩ የለበሱትን ሸለሙት። በአካባቢው ከነበሩ ሰዎች መካከል

"ይህ መንገደኛ ሐቅ አልተናገረም! ሩሚ እሱን ማመን አልነበረባቸውም" ሲል አንሾካሾከ።

"እውነት እና ውሸትን መለየት አቅም የሌለኝ ይመስልሃል? ሩሚ ሹክሹክታውን ሰምተው መለሱለት

" የተናገረው እውነት ቢሆን ካባዬን ብቻ ሳይሆን ሕይወቴን ጨምሬ እሰጠው ነበር" አሉ።

"በታጋሽ ጆሮ አድምጥ፣ በርኅራኄ ዐይን ተመልከት፣ በፍቅር ቋንቋ ተናገር"

ዘርቁቢ

1250 እ.ኤ.አ ሩሚ በኮንያ አደባባዮች ብቻቸውን እየተዘዋወሩ ነበር። ድንገት ከገበያው መሃል "ክል" "ክል" የሚል የተለምዶ ድምፅ ሰሙ። ወርቅ ሰሪው በቅርፅ ማውጫ ውስጥ ያሉትን ቁርጥራጮች በመዶሻ እያስተካከለ ነው። ከመዶሻው የሚወጣ ድምፅ የፈጠረው ሙዚቃ ሩሚን ከሱቁ ደጃፍ ቆመው እንዲቀሩ አስገደዳቸው። ታላቁ ሰው ሩሚ ከፊት ለፊቱ በመኖራቸው እጅግ የተደሰተው ሰላሑዲን ዘርቁቢ ወርቁን መቀጥቀጥ አልገታም። በመዶሻው ይነርተዋል። ወርቁ ወደ ዱቄትነት ተቀየረ፡ እንደ አመድ ብንን አለ። ዘርቁቢ ወርቁን ቢያጣም ከማዕድን በላይ ውድ የሆነ ነገር ማግኘት ቻለ - የሩሚን ጓደኝነት። ለቀጣዮቹ ዘጠኝ ዓመታት ዘርቁቢ የመውላና ሩሚ ቅርብ ወዳጅ ለመሆንም በቃ።

Edit with WPS Office

ሩሚ ለአዲሱ ጓደኛቸው ደህንነት አብዝተው ይጨነቃሉ። ዘርቁቢ የሸምስን ዓይነት እጣ እንዳይገጥማቸው ይሰጋሉ። የጓደኝነት ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ ወንድ ልጃቸውን ከዘርቁቢ ሴት ልጅ ጋር በትዳር አጣምረው ቤተሰብ ሆኑ። የሸምስ እና ዘርቁቢ ማንነትና ባሕሪ አራንባና ቆቦ ነው፡ ሁለቱ ዋልታዎች ጫፍ ላይ እንደሚኖር ፍጥረት ፍፁም የማይገናኝ ስብእና። ሻህ ወለድ እንዲህ ሲል መስክሯል፦ "(ዘርቁቢ) እንደ ማንኛውም ተርታ ሕዝብ ቀላል እና ግልፅ ሰው ነበር። አንድ ሰው ፋቲሓን እንዲቀራለት ቢጠይቀው በአግባቡ አሳምሮ ላይቀራ ይችላል"

ሩሚ ከ'ንዲህ ዓይነቱ 'ማይም' ጋር ጓደኝነት መመስረታቸው ብዙዎችን ግራ ያጋባ ነበር። የሰዎችን ውስጣዊ ውበት እንጂ አላፊ ጠፊ የሆኑ ሀብት፣ እውቀት እና ዝናን የመሰሉ ብልጭልጮችን ሩሚ አልተመለከቱም። ሌሎች ቀላል ሕይወትን ፣ ትህትና እና ቅንነትን ከግምት ላያስገቡ ይችላሉ ለሩሚ ግን እኚህ መመዘኛዎች ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ። "ላያዊ ባሕሪ ወይም ንግግር ላይ ሚታየውን ክፍል አንመለከትም። ውስጥ የተቀመጠውን እና ልበ-ስስነትን እናያለን" ይላሉ።

በዘርቁቢ ጓደኝነት ሩሚ ልባቸው ቢረጋም ሸምስን ግን መርሳት አልሆነላቸውም። ዳግም የሚገናኙበትን ቀን ይናፍቃሉ። በምናባቸው ይስላሉ። እናም ሸምስን ፍለጋ ወደ ሶሪያ አቅንተው አሰሳ ጀመሩ። በደማስቆ ጎዳናዎች፣ ሜዳ ተራራዎች፣ ዋሻ ሸለቆዎች... ያላዳረሱት ቦታ አልነበረም። ሸምሴን ያያችሁ እያሉ ያልጠየቁት የከተማዋ ነዋሪም የለም። በሊቅነቱ ዓለም ያወቀው መምህር አንድ ተጓዥ ደርዊሽ ፍለጋ እንዲህ በመንከራተቱ ያልተደነቀ አልነበረም። ሩሚ ከሸምስ ያገኘው ምንድን ነው? ለምን ይሆን እንዲህ ሚባክነውና ሚደክመው? ሲል ሁሉም ይጠይቃል። ነገር ግን ምላሻቸው "እንዲህ ዓይነት ሰው አይተን አናውቅም" ነበር።

Edit with WPS Office

ሩሚ ሸምስን ፈልገው ማግኘት አልቻሉም። ነገር ግን ድካማቸው መና አልቀረም። አንድ እውነት አረጋገጡ። ሸምስ የሚገኙበትን ቦታ አገኙት። ከሩሚ ልብ ውስጥ ተሸሽገው ነው ለካ የሚኖሩት! ውጫዊው ዓለም ላይ ሲፈልጓቸው የከረሙት ውስጣቸው የተቀበረውን ባለማየታቸው ነበር። ናፍቆትን፣ ውበትንና ፍቅርን እስከዛሬ ራሳቸው ተሸክመውት ነበራ የሚዞሩት።

"ውበቱን ሳሞግስ ኖርኩ (እውነታው ግን) ያ ውበት እና ግርማ እኔው ጋር ነበር"

አዲስ ማንነት

ፍቅርን መሰረቱ ያደረገ መንፈሳዊነት

ሩሚ በአዲስ ስብእና ወደ ኮንያ ተመለሱ። አሁን ከራሳቸውና ከሌሎች ጋር ሰላም ፈጥረዋል። በፊት ይናፈሱ የነበሩ ሽውራራ አመለካከቶች ቀንተዋል። ፍቅር ባመነጫቸው የሩሚ ጥበቦች ተማርከው በርካቶች አካበዋቸዋል። ተማሪዎቻቸውም ያለፉ ስህተቶችን አርመው በሙሉ ልባቸው ሐድረዋል። ከመሀከላቸው ሑሳሙዲን ቸለቢ ፊት-ቀደም ነው። ከዘርቁቢ ሕልፈት በኋላ የሩሚ ቅርብ ወዳጅ እሱ ሆኗል። ከሸምስና ዘርቁቢ ባሕሪያት አቀናጅቶ የያዘ በመሆኑ ሩሚ ሑሳሙዲንን እጅግ ወደውታል። ንፁህና ሌሎችን የሚያስቀድም ልብ በመያዙ ፅዱ መስታወት ሆኗቸዋል። ሑሳሙዲን ሁሉም የማሕበረሰብ ክፍል ይረዳው ዘንድ ሩሚ በቀላል ቋንቋ ሀሳቦቻቸውን ይገልፁ ዘንድ አማከራቸው። ሩሚም ይህን ለመቀበል የቸገራቸው አንዳች እንቅፋት አልነበረምና በኮንያ ጎዳናዎች፣ በህዝብ መታጠቢያ ቦታዎች እና መናፈሻ ስፍራዎች ንግግሮችን፣ ግጥሞችን እንዲሁም ታሪኮችን ይናገራሉ።

Edit with WPS Office

ሑሳሙዲን ደግሞ በሄዱበት እንደ ጥላ ከእግር እግር እየተከተለ ከአፋቸው የሚፈሰውን ወለላ ማር ይቀዳል። እጅግ ሪቂቅ ስሜቶች የተገለጹባቸው እኚህ ፅሑፎች ተደምረው በስተመጨረሻ መስነቪ ተባሉ። የሑሳሙዲን ልፋት ውጤት ለሰው ልጆች ያበረከተው ትልቁ ስጦታም ሆነ። የዚህን ቅን ተማሪ ጥረት የሚያደንቁት ሩሚ ዲያኡል ሐቅ (የእውነት ብርሃን) እያሉ ነበር የሚጠሩት።

የጭለማው_ዝሆን

ጥንታዊ የሂንዱ አዳኝ ነው የክስተቱ ተዋናይ። ሲዋልል የያዘውን ትልቅ ዝሆን ይዞ ወደ መንደሩ ይዘልቃል። ዝሆኑን በአንድ ጭለማ ክፍል ውስጥ አስሮ ጓደኞቹን ይዞ ይመለስና "ምን ይዤ እንደመጣሁ ገምቱ" ይላቸዋል። በጨለመው ክፍል ውስጥ የታሰረውን ዝሆን በየተራ መዳበስ ይጀምራሉ

የመጀመርያው ሰው የዝሆኑን ጭራ በመያዝ "አቤቱ ይዘህ የመጣኸው እንስሳ ቅጥነት"ይላል

ሁለተኛው ዳባሽም የዝሆኑን ኩምቢ በመያዝ "ይሄ ነገርማ ቅጥነት ብቻ ኣይደለም እንደ ምሶሶ የቆመ ነገር ጭምር ነው" ይለዋል።

እንደአጋጣሚ ሆኖ ሶስተኛው ሰው የዚህን ግዙፍ ዝሆን ጀርባ ይዳብሳል። "ምነው ጓዶች ይሄማ እንደ አለት የጠነከረ ዘርጣጣ ፍጥረት ነው እንጂ" ይላቸዋል።

ይህንን ትእይንት ያስተዋለው የዝሆኑ ባለቤት ግን ገለል ብሎ ቆሞ በውስጡ የሚከተለውን ይላል

"ብርሃን ቢኖር ኖሮ ይሄ ሁላ ውዝግብ ባልተፈጠረ"

ጀላሉዲን አል ሩሚ ምን ማለት ፈልገው ይመስላችኋል?

Edit with WPS Office

ሁሉም ሰው ባገኘው ነገር ተመርኩዞ እንጂ ቀዳሚ እውቀት ኖሮት ፍርድ አይሰጥም! በእጅህ ትዳብሳለህ እንጂ አታካልልም። በአይንህ ውጪውን እንጂ ውስጡን አታይም። እናም ሁሉንም ክፍል አጥርተው ሳያውቁ ለመናገርና ለመፍረድ መጣደፍ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍ ያለ ነው።

በአጭር ጊዜ ውስጥ ሩሚ ብጹእ፣ ገጣሚ፣ ፈላስፋ በሚሉ መጠሪያዎች ዝናቸው ይበልጥ ናኘ። የሀገር መሪዎች እንዲሁም ሊቃውንት ታላቅ አክብሮት ይቸሯቸዋል። ተማሪዎችና መምህራን ከአራቱም አቅጣጫዎች ሩሚን ለማዳመጥና የ'ሳቸው ባልደረባ ለመሆን ይመጣሉ። ከተለያዩ የፊቅህ ትምህርት ቤቶች ለውይይት የሚታደሙትም እንዲሁ ቁጥራቸው በየጊዜው እያሻቀበ ነው። መስነቪ 1261 ተጀምሮ 1273 ማለትም መውላና ሩሚ እስትንፋሳቸው እስከተቋረጠበት ድረስ ጊዜ ፈጅቷል። የቀብር ቤታቸውም ቱርክ - ኮንያ በአረንጓዴ ቁባ አሸብርቆ ይገኛል። ቀብራቸው ላይም እንዲህ ተከትቧል

"ስንሞት ቀብራችንን ምድር ላይ አትፈልጉት፡ በሰዎች ልብ ውስጥ ኑረን ታገኙናላችሁ"

ጀላሉዲን ሩሚ መውላና ወይም ሰይዱ-ዓሺቂን በመባል ይታወቃሉ። የአፍቃሪያን አይነታ በህይወታቸው ውስጥ ለፍቅር፣ ለመንፈሳዊ መቻቻል፣ ለመልካም ሥነ ምግባር ትልቅ ትኩረት ሰጥተው አስተምረዋል። ከጠፊዋ ዓለም ቆሻሻዎች ሁሉ ነፍስ እንዲያጸዳ ጥሪ ኣቅርበዋል። ግጥሞቻቸው በመላው ዓለም ለዘመናት ሳይረሱ እስኪንፀባረቁ ድረስ ሕዝብ ልብ ውስጥ ሰርገዋል።

የፋርስ ቁርኣን ሲሉ የሰየሙት መስነቪ በስድስት ቅፅ የተከተበ ሲሆን በሀያ ሶስት ቋንቋዎች ተተርጉሞ በብዙ ሚሊየን ኮፒዎች ተሸጧል። ግጥሞቹ አላህን በሙሉ

Edit with WPS Office

ልብ የማፍቀር ግብ ላይ መድረስ የሚቻልባቸውን መንገዶች ጠቋሚና አድራሽ ናቸው ይላሉ አስተያየት ሰጪዎች።

አራት ሰዎች ነበሩ። እነዚያም ሰዎች ግሪክ፣ ፋርሲ (ኢራናዊ)፣ ዐረብ እና ቱርክ ነበሩ። የሚፈልጉትን ነገር ይገዙበትም ዘንድ የተወሰነ ገንዘብ ተሰጣቸው። ግሪኩ “እኔ ስታፊል አምሮኛል፤ ስታፊል ግዙልንና እንብላ" አለ።

ፋርሲው “የምን ስታፊል? ኡዙም ግዙልን እንጂ ሰዎች” አለ።

ሶስተኛው “አረ ወደዚያ! ኢነብ ነው የምንገዛው፤ ኢነብ መግዛት አለብን” በማለት ተናገረ።

ቱርኩ “እንዴ! አንጉር ነው መግዛት ያለብን፤ አንጉር እንጂ ሌላ ነገር አትግዙብን” አለ።

አራቱ ሰዎች ተከራከሩ። ተነታረኩ። በጭራሽ ሊግባቡ አልቻሉም። እንዲህ እየተወዛገቡ ሳለም አንድ መንገደኛ መጣ። “ምንድነው የሚያጨቃጭቃችሁ?” በማለት ጠየቃቸው። ጉዳዩን ነገሩት። ሰውየውም “በዚህ ፍራንክ የሁላችሁንም ፍላጎት ማሟላት ይቻላል” አላቸው። ሰዎቹም “እንዴት?” በማለት ጠየቁት። ሰውዬም ገንዘቡን እንዲሰጡት ጠየቃቸው። እነርሱም እንደተባለው አደረጉ።

መንገደኛው ሰውዬ በአካባቢው ከነበረ የፍራፍሬ መሸጫ ገብቶ አንዱን የፍራፍሬ ዓይነት ገዝቶ ሲወጣ አራቱ ሰዎች ተያዩ። በዚያው በሳቅ ፈረሱ። ለካስ አራቱም የአንዱን ፍራፍሬ ስም በየቋንቋቸው እየጠሩት ነበር! አራቱም “ወይን እፈልጋለሁ” እያሉ ነበር የሚከራከሩት።

ሩሚ ከሰባት መቶ ዓመታት በፊት የጻፉት ወግ ዛሬም ድረስ እውነት ሆኖ ይሰራል። ዛሬም አንድ ዓይነት ፍላጎት ያላቸው ሰዎች ፍላጎታቸውን በሚገልጹበት መንገድ ብቻ

Edit with WPS Office

ይነታረካሉ። ዛሬም ሰዎች ተመሳሳይ ግብ ኖሯቸው በስልት ብቻ ይወዛገባሉ። ከዚህ እልፍ ሲልፍም አንድ ዓይነት ግብ የሚያልሙ ነገር ግን በስልት የሚለያዩ ሰዎች፣ ቡድኖች፣ ክበቦች፣ ማህበራት፣ ፓርቲዎች ወዘተ... እስከ መገዳደል የሚደርሱበት ሁኔታ ይከሰታል። ከሁሉም ዘንድ የጠፋው በሩሚ ወግ የተጠቀሰው የአስታራቂው መንገደኛ ቢጤ ነው።

‹‹ፍቅር በሁሉም ቋንቋዎች ውስጥ ራሱን የሚገልጥበት ውብ መንገድ አለው››

የፐርሺያ ታላቅ ገጣሚ፣ የተሰውፍ መምህርና ሊቅ የሆኑት መውላና ሩሚ ግጥሞቻቸው እጅግ ጥልቅ የሆነውን የነፍስን ዳርቻዎች የመዳሰስ ብቃታቸው ከፍ ያለ ነው። ከምንም በላይ ፍቅርን በጥልቀት ይሰብካሉ፡ በእያንዳንዳችን ውስጥ ያለን ድንቅ ውበትን እንድናስተውል፣ ህይወትን በበጎ ጎን እንድንኖራት ያመላክቱናል፣ ራሳችንን እንድናከብር ያሳስቡናል። የታላላቅ እውቀቶች መነሻ ራስን ከማወቅ እንደሚጀምሩም ያስገነዝቡናል። እጅግ ውበትን በተላበሱ ከ40 ሺህ በላይ በሚሆኑ ውብ ግጥሞች እና ምሳሌያዊ ምክሮች ዘመንን ተሻግረው እስካሁንም በሚወደዱ ስራዎቻቸው ውስጥ ይህን ሁሉ ድንቅ ጥበብ አስቀምጠውልን አልፈዋል።

አምላኬን እንዲህ አልኩት

"አላህ ሆይ! አንተን ሳላውቅማ አትግደለኝ!"

አላህም እንዲህ መለሰልኝ

"እኔን ያወቀ ሰው አይሞትም!"

Edit with WPS Office

ምንጮች

40 rules of love, Elif Shafak

Mathnawi ma'nawii VII

Mawlana Jalaluddin, Trinath Mishra

Articles about Rumi...

Edit with WPS Office